**የተከበሩ አቶ ይርሳው ታምሬ!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 6 (2) (ሐ) እና አንቀጽ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልጽ አጭር ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የሚደነግግ በመሆኑና ይህን ሪፖርት ለማቅረብ ዕድሉን በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ እየገለፅኩ፤ መ/ቤታችን በ2008 እና 2009 ኦዲት አድርጎ ያጠናቀቃቸውን የ10 መ/ቤቶች መደበኛ የክዋኔ ኦዲት እና የ7 መ/ቤቶች የክዋኔ ክትትል ኦዲት በአጠቃላይ ዘገባ ሪፖርት የሐተጠናቀሩ ቢሆንም ከጉልህነት እና ጊዜን ለመመጠን ሲባል በዘገባ ሪፖርቱ ከተዘጋጁት ከመደበኛ የክዋኔ ኦዲቶች መካከል የ8ቱን እና ከክትትል ኦዲት ሪፖርቶች ደግሞ የ3ቱን ዋና ዋና ግኝቶች ብቻ በንባብ አቀርባለሁ፤
2. የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ስራዎች በተመደበላቸው ሃብት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣በቅልጥፍና እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በማከናወን የተቋቋሙበትን ዓላማ ማሳካታቸውን ለማረጋገጥ የሚከናዎን ኦዲት ሲሆን የክትትል ኦዲት ደግሞ ቀደም ሲል በክዋኔ ኦዲት ታይተው ሪፖርት በተላለፈላቸው መሰረት ለግኝቶቹ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ ኦዲት ተደራጊዎች የእርምት እርምጃ በመውሰድ ማስተካከያዎች ስለማድረጋቸውና ግኝቶቹ ያሉበት ሁኔታ የሚረጋገጥበትና የተጠያቂነት አሠራር ያለበት ሁኔታ የሚፈተሽበት የኦዲት ዓይነት ነው፡፡

   የእያንዳንዱ ኦዲት ውጤት የያዘ ሪፖርት አስቀድሞ ለየመቤቶቹና ለተቆጣጣሪ አካላት የማሻሻያ አስተያየት ያካተተ ዝርዝር ሪፖርት እንዲደርሳቸው አድርገናል፡፡ ኦዲት ተደራጊዎችም ያላቸውን አስተያየትና ምላሽ ሰጥተዋል፡፡
3. ለክዋኔ ኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዘርፎቹ እንዲመሩባቸው መንግስት ያወጣቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፤ ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤቶች በህግ የተሰጧቸው ስልጣንና ተግባራት፣የየመ/ቤቶች የስራ ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንዳስፈላጊነቱ ከየመ/ቤቶቹ ደንበኞች/ ተገልጋይች ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በኦዲት ስራው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የኦዲት ስራውም ዓለም አቀፍ እና ብሔራዊ የክዋኔ ኦዲት አሰራር መርሆችና ስታንዳርዶችን ተከትሎ የተከናወነና ግኝቶቹም አስተማማኝና ተጨባጭ ማስረጃዎች ያሏቸው ናቸው፡፡በአጠቃላይ በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ግኝቶች በናሙና በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች ብቻ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባ እያሳሰብኩ ከዚህ በመነሳት ዋና ዋና ግኝቶችን በአጭሩ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

1. **የክልሉ የስርዓተ ፆታና ወጣቶች ጉዳይ ስርፀትንና ተጠቃሚነት በተመለከተ፤**

***የወጣት ማዕከላትና ስነ-ምግባርን በተመለከተ፣***

4. ***ወጣቱ በመዝናኛ እጦት ችግር አልባሌ ቦታ በመዋል የአጓጉል ሱስ ተጠቂ እንዳይሆን በክልሉ ውስጥ ደረጃቸውን የጠበቁ የወጣት ማዕካላትን በመገንባት አገልግሎት ላይ ማዋል እንዲሁም ወጣቱ ብቁ አገር ተረካቢ ዜጋ እንዳይሆን እንቅፋት የሚፈጥሩ አሉታዊ የስነ-ምግባር ችግሮች እየተጠኑ መፍትሄ ሊሰጣቸው የሚገባ ቢሆንም፡***

- *ከ2004 እስከ 2007 (9 ወር) ባሉት ተከታታይ በጀት ዓመታት፣እንደቅደም ተከተላቸው በክልሉ ውስጥ በአዲስ መልክ እየተገነቡ ያሉት የወጣት ማዕከላት ቁጥር አፈፃፀም ከዓመት ወደ ዓመት ቁጥራቸው መጨመር ሲኖርበት እየቀነሰ መምጣቱ፣ (106.8%፣17.5%፣11.6% እና 4.2%)*

- *ከ2005 ጀምሮ ለ3 ተከታታይ አመታት የማዕከላት መገንቢያ ቦታ ርክክብ ለማድረግ ከታቀደው 38.9%፣48.8% እና 55.6% እንደቅደም ተከተላቸው ዝቅ ያለ አፈፃፀም ያላቸው መሆኑ፣*

- *ማዕከላትን በቁሳቁስ ለመደገፍ ከታቀደው 79.4 %፣ 48.8 %፣ 21.3 % እና 18.2 % እንደቅደም ተከተላቸው የተፈፀመ ሲሆን ክንውኑ ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰ መምጣቱ፣*
- *ማዕከላትን በገንዘብ ለመደገፍ ከታቀደው 59.2 %፣40.9%፣41.7% እና 32.3% እንደቅደም ተከተላቸው የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ዝቅተኛ መሆኑ፣*
- *በክልሉ ውስጥ ከተገነቡት 451 የወጣት ማዕከላት ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት 206 /45.7%/ ብቻ ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ 245 /54.3%/ ማዕከላት አገልግሎት የማይሰጡ፤ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር/ ካርታና ፕላን የተሰጣቸው ማዕከላት ብዛት 234 /52%/ ብቻ ሲሆኑ፤ቀሪዎቹ 217 /48%/ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዳልተሰጣቸው በኦዲት ወቅት ለቀረበ መጠይቅ ምላሽ ላይ መገለፁ፣*
- *በሌላ በኩል የክልሉን ወጣቶች የመጪው ዘመን ብቁ አገር ተረካቢ ዜጎች እንዲሆኑ በተለያየ መልኩ የሚገለፁ የስነ-ምግባር ችግሮች ያሉበትን ደረጃ ቢሮው አጥንቶ የመፍትሄ አቅጣጫ ያላመላከተ መሆኑ፣*
- *በሌላ በኩል በክልሉ ውስጥ የዝሙት አዳሪነት ደረጃ ምን ላይ እንዳለ መረጃ እንዲሰጡን የክልሉን ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ብንጠይቅም፤ቢሮው በወረዳ ደረጃ በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ጽ/ቤቶች ያሉት በመሆኑ በዚህ ዙሪያ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ችግር ስለተፈጠረበት በአሁኑ ወቅት ዝሙት አዳሪነት እየጨመረ ይሁን እየቀነሰ ስለመገኘቱ እና ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት እንዳልተከናወነና መረጃ እንዳልተያዘ መገለፁ፣*
- *በክልሉ ውስጥ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ላሉ የትምህርት ተቋማት ሴቶችንና ወጣቶችን አስመልክቶ የቀረበ መጠይቅ ላይ፣በዩኒቨርስቲዎች እና በት/ቤቶች አካባቢ ለወጣቶች የስነ-ምግባር ችግሮች መከሰት ምክንያት የሚሆኑ ጫት፣ሽሻ፣ ጭፈራ እና ጠላ ቤቶች መኖራቸውና በሚመለከታቸው አካላት ችላ ተብለው የሚታዩ መሆኑ፤*
- *የስርዓተ ፆታና የስነ-ተዋልዶ ስልጠና ለተማሪዎቻቸው እንደሚያስፈልጋቸው መጠይቅ የቀረበላቸው ት/ቤቶች የገለፁልን ሲሆን፤ነገር ግን ስልጠናውን አግኝተው እንደማያውቁ፣ጉዳዩን የተመለከቱ ብሮሸሮችና ፓምፌሌቶች እንኳን ትኩረት አድርጎ የሚሰጣቸው አካል አለመኖሩ፤ከዚህ ጋር በተያያዘም ለዩኒቨርስቲዎች የቀረበ መጠይቅ ላይ ከ5ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ስነ-ተዋልዶንና ስርዓተ ፆታን የተመለከቱ ጠንካራ የግንዛቤ ማስጨበጫ*

ስልጠናዎች ቢሰጡ ወደ ተቋማቱ ከገቡ በኋላ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በእጅጉ መቀነስ እንደሚቻል መጠቆማቸው ይጠቀሳሉ፡፡

5. **በክልሉ ውስጥ በከተማና በገጠር ለሚገኙ ስራ-አጥ ወጣቶች በተለያዩ መስኮች ቋሚ እና ጊዜያዊ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ማድረግ ተገቢ ቢሆንም፡፡**

- ከ2004 እስከ 2007 (9ወር) ድረስ በጥቅል / በቋሚና ጊዜያዊ/ የተፈጠሩትን የስራ እድሎች ሊጠናቀቅ 3 ወራት ብቻ በሚቀሩት ስትራቴጅክ እቅድ አንፃር ሲታይ በድምሩ 2,858,136 ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድሎችን ለመፍጠር ታቅዶ 1,680,628 (58.8%) የስራ እድሎች የተፈጠሩ ሲሆን ክንውኑም በቂ እና ችግሩን በሚፈታ ደረጃ አለመሆኑ፣
- በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ በከተማና በገጠር በተለያዩ ሴክተሮች ለስራ አጥ ወጣቶች በተፈጠሩ ጊዜያዊ የስራ እድሎች (709,041) ወጣቶች ከሚያገኙት ገቢ ከ5% ጀምሮ እንዲቆጥቡ በማድረግ ከ75% በላይ የሚሆኑት ወደ ቋሚ የስራ መስክ እንዲሰማሩ ለማድረግ በግብ ደረጃ የተቀመጠ ቢሆንም፤በአፈጻጸሙ ዙሪያ አግባብ ያለው መረጃ ያልተያዘና አፈፃፀሙ የማይታወቅ መሆኑ፣
- በሌላም በኩል ከክልል፣ዞንና ወረዳዎች ላይ ለሚገኙ የሴቶች፣ወጣቶችና ህፃናት መ/ቤቶችና ሌሎች ተቋማት የወጣቶች ስራ እድል ፈጠራን በሚመለከት የቀረቡ መጠይቆች ላይ፤

✓ በክልሉ ውስጥ ሴቶችና ወጣቶች ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና በሚፈለገው መጠን ወደ ስራ ሊያሰማራቸው የሚያስችል በተለየ ትኩረት የሚያበረታታ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና በቂ የሆነ የብድር አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችል የብድር ስርዓት በሚገባ ተግባረዊ አልተደረገም የሚሉትን ዋና ዋና ግኝቶች መሰረት በማድረግ የስርዓተ ጾታና ወጣቶች ጉዳይን አስመልክቶ የሚመለከታቸው ሁሉ ርብርብ በማድረግ አካቶ መስራትና የስራ አጥነትን ችግሮች ለመቅረፍ ጥረት መደረግ እንዳለበት በዝርዝር ሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

*2.* **የገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በራስ ሃይል የሚገነቡ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በሚመለከተ**

6. **ኤጀንሲው በኪራይ የሚያስገባቸው ማሽንና ተሽከርካሪዎች በውላቸው መሰረት፣የሚከፈላቸው የኪራይ ክፍያም በትክክል የሰሩበት ሰዓት እየተመዘገበ ስለመከፈሉ ለማረጋገጥ በተደረገ ኦዲት፣**

- በ4 ፕሮጀክቶች በኪራይ ለገቡ 22 ማሽነሪዎች የተሞላላቸው ነዳጅ ማሽነሪዎች የሰሩበት ተብሎ ለተያዘው ሰዓት የማያሰራ በመሆኑ መስራት ከሚችሉት ሰዓት በላይ ሰሩ ተብሎ የተከፈላቸው የኪራይ ክፍያ ብር 7,928,338.00 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- **በታች ጋይንት- መቅደላ** መንገድ ስራ ፕሮጀክት- ከ2003-2006 በጀት ዓመት የተለያዩ በኪራይ የገቡ ተሽከርካሪዎች በፕሮጀክቱ የሰሩበት ሰዓት መረጃ ባለመገኘቱ ምን ያህል ገንዘብ እና በሰሩት ልክ እንደተከፈላቸው ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ዳባት ጃናሞራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት- ፕሮጀክቱ በ2005 ለ6 ማሽኖች ብር 58,137.50 እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት ለ8 ማሽኖች ብር 45,397.70 በድምሩ ብር 103,535.20 ለኪራይ ተሽከርካሪዎች በተለያየ ምክንያት ስራ ላልሰሩበት ጊዜ 50% ክፍያ የከፈለ መሆኑ በመረጋገጡ በግኝቶቹ ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ በሪፖርታችን ዝርዝር አስተያየት አስተላልፈናል፡፡

7. **ለተሸከርካሪዎችና ማሽነሪዎች የሚሰራጨው ነዳጅ፣ዘይትና ቅባት በተገቢው መለኪያና መንግስት ባወጣው የኖርማላይዜሽን መመሪያ መሰረት ጥቅም ላይ ሊውል ሲገባ፤**

- ኤጀንሲው ለተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች የሚያሰራጨው ነዳጅ፣ዘይትና ቅባት ደረጃውን በጠበቀ መስፈሪያ እየተለካ መንግስት ባወጣው የኖርማላይዜሽን መመሪያ መሰረት ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተውለዋል፡፡

**ታች ጋይንት መቅደላ መንገድ ስራ ፕሮጀክት፤**

- ፕሮጀክቱ ከ2003 እስከ 2007 በጀት ዓመት የተረከበውን ነዳጅ በትክክል ስራ ላይ ስለማዋሉ የሚያስረዳ ማስረጃ ባለመገኘቱ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በ2005 በቁጥር 4፣በ2006 በቁጥር 3 እንዲሁም በ2007 በቁጥር 4 የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸው ኦፕሬተሮች ቢኖሩም አንድም ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ የሌለው መሆኑ፤

**ዳባት ጃናሞራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት**

- በ2005 በጀት ዓመት አንድ መለያ ቁጥሩ 0351 የሆነ ሎደር 950 ሰዓት ሰርቶ 14863 ሊትር ነጃጅ እንደተጠቀመ መረጃ ቢገኝም ኖርማላይዜሽን የተወሰነበት መረጃ ባለመገኘቱ የነዳጅ አጠቃቀሙን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በ2006 በጀት ዓመት አንድ መለያ ቁጥሩ የማይታወቅ ሮለር 16751 ሊትር ነጃጅ እንደተጠቀመ ማስረጃዎች የሚያረጋግጡ ቢሆንም የሰራው ሰዓት የሚያሳይ ማስረጃ ባለመገኘቱ የነዳጅ አጠቃቀሙን ማረጋገጥ አልተቻለም፤
- በ2007 በጀት ዓመት አንድ መለያ ቁጥሩ የማይታወቅ ሮለር 617.3 ሰዓት ሰርቶ 3885 ሊትር ነጃጅ እንደተጠቀመ መረጃ ቢገኝም ኖርማላይዜሽን የተወሰነበት መረጃ ባለመገኘቱ የነዳጅ አጠቃቀሙን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ

**መተማ አብርሀጅራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት**

- ፕሮጀክቱ ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመት የተረከበውን ነዳጅ በትክክል ስራ ላይ ስለማዋሉ የሰራበትን ሰዓት የሚያሳይ ተያያዥ ማስረጃ ባለመገኘቱ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በ2007 በጀት ዓመት በፕሮጀክቱ ከነበሩና የሰሩት ሰዓት/የሄዱት ኪ.ሜ እና የተጠቀሙት ነዳጅ ማስረጃ ከቀረበላቸው 26 ተሽከርካሪዎች ውስጥ 7 ተሽከርካሪዎች ኖርማላይዜሽን የተወሰነላቸው ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የነዳጅ አጠቃቀማቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

**ደብረ ማርቆስ ኤልያስ ሎት 1 መንገድ ስራ ፕሮጀክት**

- በ2006 በጀት ዓመት 20 ተሽከርካሪዎች ኖርማላይዜሽን ያልተሰራላቸው በመሆኑ የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ አጠቃቀም ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በ2005 ዓ.ም አንድ መለያ ቁጥሩ ዲ155 የሆነ ዶዘር በሰዓት እስከ 120.58 ሊትር፣ አንድ መለያ ቁጥሩ የማይታወቅ ኤክስካቫተር በሰዓት እስከ 66.38 ሊትር ተጠቅመው የተገኙ ቢሆንም አጠቀቀማቸው በኖርማላዜሽን ባለመለካቱ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፤
- በ2006 በጀት ዓመት አንድ መለያ ቁጥሩ 502073 የሆነ ዶዘር 46,355 ሊትር ነጃጅ እንዲሁም መለያ ቁጥሩ 508083 የሆነ ሮለር 10,590 ሊትር ነዳጅ እንደተጠቀሙ መረጃ ቢገኝም የሰሩበትን ሰዓት የሚያሳይ ማስረጃ ባለመገኘቱ የነዳጅ አጠቃቀማቸውን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

- በ2006 አንድ መለያ ቁጥሩ PY220C የሆነ ግሬደር በሰዓት እስከ 92.01 ሊትር ተጠቅሞ የተገኘ መሆኑ፤

**ቁጭ አየሁ ዚገም መንገድ ስራ ፕሮጀክት**

- በ2006 በጀት ዓመት የራስ ሃይል ተሽከርካሪዎች ምን ያህል ሰዓት እንደሰሩ የማይታወቅ በመሆኑ የነዳጅ አጠቃቀማቸውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- ፕሮጀክቱ ከ2003-2005 በጀት ዓመት የተረከበውን ነዳጅ በትክክል ስራ ላይ ስለማዋሉ ማስረጃ ባለመገኘቱ ማረጋገጥ አለመቻሉ በሚሉት ግኝቶች ላይ ተገቢውን ዝርዝር አስተያየት ሰጥተናል፡፡

**3. የከተሞች ፅዳት፣ውበትና አረንጓዴ ልማት ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ፤**

**8. የከተሞች አንዱና አሳሳቢ ችግር የአካባቢ ንፅህና (ጉድለት) ነው፡ የአካባቢ ችግር መንስኤው በርካታ ቢሆንም በተገኘው ቦታ ሁሉ መፀዳዳት፣ ቆሻሻ መጣልና ማቃጠል እንዲሁም መጸዳጃ ቤትን ከቦዮች፣ ተፋሰስ መስመሮችና የውሃ አካላት(ወንዞችና ሃይቆች)ማገናኘት ለጤና አደገኛና የአካባቢ ጠንቅ ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተዳምሮ የመፀዳጃ አገልግሎቶች አለመሟላት፣የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎቶችና መሠረተ ልማቶች አለመኖር ችግሩን በእጅጉ ያባብሰዋል፡፡**ለአብነትም፤

**በባህርዳር ከተማ አሰተዳደር፤**

- መጸዳጃ ቤታቸውን ከተፋሰስ ጋር ያገናኙና ከመኖሪያ ቤቶችና ከድርጅቶች የሚወጣን ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ጣና ሃይቅና አባይ ወንዝ የሚለቁ ነዋሪዎችና ድርጅቶች መኖራቸዉ፣/ለምሳሌ፤ ፓፒረስ፣ሆምላንድ፣ ባህርዳር፣ ግራር፣ አቫንቲ ሆቴልና የባህር ዳር ማረሚያ ቤት መጸዳጃ ቤታቸውን ከጎርፍ ማፋሰሻ ቦይ እና ከጣና ሃይቅ ጋር ያገኛኙ መሆናቸው፣
- አንድ የህብረት ስራ ማህበር በሰፈነ ሰላም ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 በሚገኘው የንግድ ተቋሙ የሚመነጨውን የዓሳ እጣቢና የተለያዩ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ወደ አስፓልት መንገድ የሚደፋ መሆኑ፣
- በቀበሌ 06 ግሽ አባይ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው በሆቴሉ እና በሆቴሉ ምስራቅ በኩል በተሰሩ ኮንቴነሮች መካከል በሚገኘው ክፍት ቦታ ጨለማን ተገን በማድረግ ለመጸዳጃ አገልግሎት እየዋለ መሆኑ፣

**በደሴ ከተማ አስተዳደር**

- ከፒያሳ ወደ ተቋም በሚወስደው የአስፓልት መንገድ ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ደሴ ቅርንጫፍ ፊት ለፊት ከሚገኘው የአስፓልት መንገድ ዳር የጎርፍ ማፈሰሻ ቦይ ተደፍኖ የተገኘ መሆኑ፣
- በደረቅ ቆሻሻ አስወጋጅ ማህበራት በኩል በየመንገዱ መነሳት የሚገባቸው የተሰበሰቡ ቆሻሻዎች በወቅቱ ያለመነሳት ችግር መኖሩ፣
- በከተማዉ ዋና ዋና መንገድ የሚገኙ የመፋሰሻ ክዳኖች ተከፍተው የሚገኙ፣ አንዳንድ ክዳኖች የተሰባበሩና ክዳን የሌላቸው በመሆኑ ተንቀሳቃሾችን ለተለያዩ አደጋዎች ያጋለጡ መሆኑ፤
- በፒያሳ ክፍለ ከተማ ከ1ኛ ፖሊስ ጣቢያ እስከ ኔት ወርክ ካፌ ያለውን የአስፓልት መንገድና ማፋሰሻ ቦይ በቅርብ ከሚገኙ የመኖሪያ ቤቶች የሚወጣዉ የመጸዳጃ ፍሳሽ በአስፓልቱ ላይ የሚፈስ መሆኑ፣
- የቤቶች ልማት ንዑስ ቀበሌ 012 መነሃሪያ ሳይት፣ ንዑስ ቀበሌ 14 አሬራ ሳይት፣ ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል እና ደሴ ቄራ አገልግሎት ተደጋጋሚ የፍሳሻ ቆሻሻ ችግር ያለባቸው መሆኑ፣
- በመናፈሻ ክፍለ ከተማ መናፈሻ ሳይትና ቧንቧ ውሃ ክፍለ ከተማ ካራጉቱ ሳይት ከሚገኙ የጋራ

መኖሪያ ቤቶች የሚወጣው የፍሳሽ ቆሻሻ በዋና መንገድ ላይ እየፈሰሰ የሚገኝ መሆኑ፣

- ቦርከና ወንዝ ላይ ከተለያዩ ሰፈሮች የተሰበሰበ ደረቅ ቆሻሻ እየተደፋ የሚገኝ መሆኑ፣ በተለያዩ ቦታዎች ደረቅ ቆሻሻዎች በተገኙበት አካባቢ የሚቃጠሉ መሆኑ፤

**በጎንደር ከተማ አስተዳደር**

- በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የግንባታ ተረፈ ምርት፣ የጋራጅ ቆሻሻዎችን፣የብር ጭቅ ስብርባሪዎችና ሌሎችንም ቆሻሻዎች የሚደፉበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የእስልምና ጉዳዮች ባስገነባው ሀሊፍ ህንጻ የሚኖሩ ነዋሪዎች የሚጠቀሙበትን ፍሳሽ ቆሻሻ (ሴፕቲክ ታንክ) ነዋሪዎች በማይኖርበት ጊዜ ከቱቦ እና ከተፋሰሶች ጋር የሚያገናኙ መሆኑ፣
- ከተለያዩ ህንጻዎች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን ወደ ተፋሰስ እና ወደ ተፈጥሮ ውሃ መፋሰሻ መልቀቅ (ኮንዶሚኒየም፣ ሆስፒታል፣ የቤቶች ልማት ቡድን እና የግል ድርጅቶች) እንዳሉ በኦዲት ወቅት በመረጋገጡ ለየግኝቶቹ አስፈላጊው ዝርዝር አስተያየት ያየዘ ሪፖርት አስተላልፈናል፡፡

9. **በከተሞች የህዝብና የአካባቢውን ደህንነት ያገናዘበ፣ ተገቢውን መስፈርት የተከተለ፣ እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ሊገነቡ፣ ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ሊጠበቁ፣ ተገቢውን አገልግሎት ሊሰጡና፣ የአካባቢ ጥበቃ ኦዲት ሊሰራላቸው ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በከተሞች ኢንዱስትሪዎችና የህክምና ተቋማት አግባብነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የቅድመ ማጣራት ሥራዎችን /Pretreatment Facilities/ እንዲሰሩና አዳዲስም ሆኑ ነባር ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እንዲያስጠኑ ማድረግ ሲገባ በኦዲት በታዩ ከተሞች** ፤(ባህርዳር፣ ጎንደርና ደሴ)

- ደረጃቸውን የጠበቁ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ያልተገነቡ፣ የነባር ደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ያልተደረገላቸው፣ አዳዲስ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ሲገነቡም ሆነ ነባሮቹ ሲሻሻሉ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ /ኦዲት/ ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
- የፍሳሽም ሆነ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን በተመለከተ የጥናት ሰነድ አለመኖሩ እና አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ቆሻሻን በቀላሉ ለማስወገድ ምቹ አለመሆ ናቸው፣
- አደገኛ /Hazardous/ የሚባሉትን ቆሻሻዎች ለማስወገድ ከተለያዩ የስራ ዘርፎች የተውጣጡ ግብረ ሃይሎች ቢኖሩም እነዚህን ቆሻሻዎች ለማስወገድ የሚያገለግሉ ቋሚ የማስወገጃ ቦታ በጥናት ያልተለየ መሆኑ፣
- በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከሰውና እንስሳት ንክኪ እንዲጠበቁ አለመደረጉ፣

**ደሴ ከተማ አስተዳደር**

- በቀበሌ 011 ልዩ ስሙ ሮብ አገር እየተባለ በሚጠራው ቦታ ላይ የተገነባዉ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለ15 ቀናት አገልግሎት ከሰጠ በኋላ ግንባታው በመናዱ አገልግሎት መስጠት ያቆመ መሆኑ፣
- ከደሴ ከተማ 2 ኪ.ሜትር ርቆ አዝዋ ገደል የሚገኘው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ያለበት ሁኔታ ለከተማ ነዋሪዎችም ሆነ ለእንስሳቶች ንክኪ የተጋለጠ መሆኑ በሚሉ ትግኝቶች ላይ ዝርዝር አስተያየታችንን በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

4. የክልሉን የኢንቨስትመንት እንቅስቀሴ በተመለከተ፤

10. በክልሉ ኢንቨስትመንት ላይ በተፈለገዉ መጠን ለተገቢዉ አካል ፍቃድ መሰጠትና ኢንቨስትመንት ፍቃዱን በወቅቱ እያሳደሱ እንዲጠቀሙበት መደረግ ሲገባው፣

በክልል ደረጃ የታየ እንቅስቃሴ፤

- የእንቨስትመንት ፍቃድ ከመስጠት አንጻር ከዓመት ዓመት በካፒታል መጠን እየቀነሰ (ከ2003-2006 ዓ.ም በተከታታይ ብር 26.6 ሚሊዮን፣ 24.6 ሚሊዮን፣ 23.2 ሚሊዮን እና 12.5 ሚሊዮን) የመጣ መሆኑንና ወደ ትግበራ የሚገቡት ፕሮጀክቶች ቁጥር የ2004 በጀት ዓመት ከ2003 በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ (25÷209 ፕሮጄክቶች=12% ብቻ) አፈጻጸም ያለዉና የ2006 በጀት ዓመት(69 ፕሮጄክቶች) ከ2005 በጀት ዓመት (98 ፕሮጀክቶች) ሲታይ የቀነሰ መሆኑን ማሳየቱ፤
- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ፍቃድ መስጠት የ2004 ከ2003 እንዲሁም የ2006 ከ2005 በጀት ዓመት አፈጻጸም አንሶ የታየበት ሁኔታ መኖሩ ወጥነት ባለዉ መልኩ ዕድገት አለማሳየቱ፤
- በ2005 በጀት ዓመት የክልሉ ዕቅድ ክንዉን አፈጻጸም ሲታይ ለ1,500 ፕሮጀክቶች ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ1,065 ፕሮጀክቶች (71%) ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን ከዚህም ዉስጥ ለ521 የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ217 (41.65%) ብቻ የተሰጠ መሆኑ፣

- የክልሉ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30/2006 ዓ.ም ድረስ ብር 157.6 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡና 1,867,747 ሰዎች የስራ ዕድል የሚፈጥሩ 8,867 ፕሮጀክቶች (ከዚህ ዉስጥ 3,284 ግብርና፤1,463 ኢንዱስትሪ፤1,727 ኮንስትራክሽን፤1,389 በሆቴልና ቱሪዝም፤522 በማህበራዊ አገልግሎቶች፤457 በንግድ፤14 በትራንስፖርትና 11 በማዕድንና ኢነርጂ ዘርፍ) የኢንቨስትመንት ፍቃድ ያወጡ ቢሆንም 1,668 (18.81%) ብቻ አገልግሎት መስጠት የጀመሩ፣909 (10.25%) ብቻ ግንባታ ላይ ያሉና ሌሎቹ በቅድመ ግንባታ ላይ ያሉ መሆናቸዉን ግንቦት 2006 ዓ.ም ቢሮ ባሳተመው መጽሄት ገጽ 22 ላይ መገለጹ፤
- በ2006 በጀት አመት በተለያዩ ቀናት የቢሮ ባለሙያዎች በባህር ዳርና በጎንደር ከተሞች ተገኝተዉ የመስክ ድጋፍ ባደረጉበት ወቅት በከተሞች ያለው የክትትልና ድጋፍ ስራ ደካማ በመሆኑ የበርካታ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ መታደስ አለመቻሉና በመረጃ የታወቁት ብቻ 1,059 ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ባለማድረጋቸዉ ፍቃዳቸዉ የተሰረዘ መሆኑ፤
- በ2005 በጀት አመት ለፕሮጀክቶቹ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ተደርጎ ወደ ተግባር የማይገቡትን ለመሰረዝ በበጀት ዓመቱ ዕቅድ ተይዞ የየዞኑን በማጠቃለል በድምሩ 406 ፕሮጀክቶች ፈቃዳቸው የተሰረዘ መሆኑ፤

ሰሜን ጎንደር ዞን ኢ/ከተማ ል/መምሪያ

- ከ2003 እስከ 2007 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠት ስትራቴጅክ ዕቅድ ሲዘጋጅ በየዘርፍ ተለይቶ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- የሰሜን ጎንደር ዞን በ2006 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠት ሁኔታ ሲታይ በካፒታል ብር 2.6 ቢሊዮን ብር ያላቸዉ ብዛታቸዉ 180 ለሆኑ ፕሮጀክቶች ፍቃድ ለመስጠት ዕቅድ የተያዘ ሲሆን 1.62 ቢሊዬን ብር (ከታቀደዉ 62.30%) ያስመዘገቡ ብዛታቸዉ 318 (ከታቀደዉ 176.6%) ለሆኑ ፕሮጀክቶች ፍቃድ የተሰጠ

መሆኑና ከካፒታል መጠን አንጻር የሚፈለገዉ ግብን እየመታን አለመሆኑ፣

- የዞኑ 2006 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሲታይ ብዛታቸዉ 27 ለሚሆኑ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ፍቃድ ለመስጠት ዕቅድ የተያዘ ሲሆን ለ14 (51.85%) ብቻ ፍቃድ የተሰጠ መሆኑ፤ ፍቃድ ካወጡ 14 ፕሮጀክቶች ዉስጥ 8 (57%) ፕሮጀክቶች ብቻ መሬት የተረከቡ መሆኑ፤በፖሊሲው ትኩረት በተሰጣቸዉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ቁጥር አናሳ መሆኑ፣
- በ2007 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የነበረዉ አፈጻጸም ሲታይ በበቂ ደረጃ እየተፈጸመ አለመሆኑን ማሳየቱ፤ ለአብነትም፡-ወደ አፈጻጸም የገቡ ፕሮጀክቶች የፈጠሩት ጊዜያዊ የስራ ዕድል 26,500 በዕቅድ ተይዞ ክንውኑ 11,488 (43.4%)፣ወደ አፈጻጸም የገቡ ፕሮጀክቶች የፈጠሩት ቋሚ የስራ ዕድል 1,954 በዕቅድ ተይዞ ክንውኑ 388 (19.9%) ብቻ መሆኑ፣
- ሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ፍቃድ መስጠት ላይ በ2003 በጀት ዓመት 64 የነበረዉ በ2004 በጀት ዓመት ወደ 10 (15%)ዝቅ ያለና ከዚያም በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመት በተከታታይ ወደ 2 እና 3 የወረደ ከመሆኑም በላይ በ2006 በጀት ዓመት 143 የተለያዩ ፕሮጀክቶች ፍቃድ የተሰረዘ መሆኑ፤

**ጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት**

- ከብር 87 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡና ለ735 የሰዉ ኃይል የስራ ዕድል የፈጠሩ 5 ፕሮጀክቶችና የካፒታል መጠናቸዉ የማይታወቅ 2 (አንዱ የጥጥ ማዳመጫና ሌላዉ የምግብ ዘይት ፋብሪካ) ፕሮጀክቶች ስራ ጀምረዉ ካቋረጡ ከ2 ዓመት በላይ የሆናቸዉ መሆኑ፤
- በ2003 በጀት ዓመት ዉስጥ 7 እና በ2006 በጀት ዓመት 6 በድምሩ 13 ፕሮጀክቶች ፍቃድ የተሰረዘ መሆኑ፤
- ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪም ፍቃድ መስጠት በዘርፍ ሲታይ ሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ላይ በ2003 በጀት ዓመት 7 የነበረዉ በ2004 በጀት ዓመት ላይ ወደ 1 እና በ2005 በጀት ዓመት 28 የነበረዉ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 8 ዝቅ ያለበት ሁኔታ መኖሩ፤

**ደቡብ ወሎ ዞን ኢ/ከ/ል/ መምሪያ**

- ደሴና ኮምቦልቻን ሳይጨምር ከ2004 እስከ 2007 ግማሽ ዓመት ባለዉ ጊዜ የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠት ከፕሮጀክት ብዛትና ከካፒታል አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ የነበረ መሆኑ፤
- በ2006 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠት ዕቅድ ክንዉን ሲታይ ብዛት 100 ታቅዶ 52 (52%) ብቻ የተሰጠ ሲሆን በካፒታል 1 ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ ባለሃብቶች ፍቃድ ይሰጣል ተብሎ የታቀደ ሲሆን ብር 446 ሚሊዮን አካባቢ (45%) ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሃብቶች ፍቃድ የተሰጠ መሆኑ፤
- በ2006 በጀት ዓመት 23 ፕሮጀክቶች ፍቃድ የተሰረዘ (16ቱ ወደ ስራ ባለመግባት፤ 4ቱ ፍቃድ በወቅቱ ባለማሳደስና ሪፖርት ባለማቅረብ፣ 3ቱ ፍቃድ በመመለሳቸዉ) ሲሆን ለ120 ባለፍቃዶች የዕድሳት አገልግሎት እንደሚሰጥ ታቅዶ ለ78 (65%) ብቻ መሰጠቱ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን፤
- በ2005 በጀት ዓመት ከፕሮሞሽን ስራ ጋር ተያይዞ በእቅድ የተያዙ ስራዎች ለምሳሌ፤በበጀት አመቱ አዲስ ፍቃድ መስጠት ለ116 ፕሮጀክቶች ዕቅድ ተይዞ ለ62 (53%) ብቻ የተሰጠና ፍቃድ ይሰረዝባቸዋል ተብሎ የተጠበቀዉ የ25 ፕሮጀክቶች ሲሆን የ31 (124%) ፕሮጀክቶች መሰረዙ እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት ፍቃድ የመስጠቱ ስራ ከታቀደዉ በታች መሆኑና ፈቃድ ባለማሳደሳቸዉ የተሰረዘባቸዉ ያሉ መሆኑ፤

- ከ2004 እስከ 2007 ግማሽ በጀት ዓመት ባለዉ ጊዜ ዉስጥ 136 የሚሆኑ የኢንቨስትመንት ፍቃዶች የሰረዘ መሆኑ፤
- ከኮምቦልቻ ከተማ አገልገሎት ጽ/ቤት የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠት ሁኔታ ሲታይ ግብርና ዘርፍ ላይ በ2004 በጀት አመት ለ6 ፕሮጀክቶች፣ በ2005 በጀት ዓመት ለ1 እና በ2006 በጀት አመት ለ2 የተሠጠ መሆኑና በ2007 ግማሽ በጀት አመት ምንም ያልተሰጠ መሆኑ፣ ለሆቴልና ቱሪዝም በ2004 በጀት ዓመት እና በ2007 ግማሽ በጀት ዓመት ድረስ ምንም አለመሰጠቱ፣ በ2005 በጀት አመት ለ5 ፕሮጀክቶችና በ2006 በጀት አመት ለ1 ፕሮጀክት መሰጠቱ ዝቅተኛ አፈጻጸም መሆኑ፤
- በ13/02/04 ዓ.ም የደሴ ከተማ አገልግለት ጽ/ቤት ባወጣዉ ማስታወቂያ ላይ ሰኞ ገባያ አካባቢ 3ኛ ፓሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት የኢንቨስትመንት ቦታ የወሰዱ 8 ግለሰቦች ወደ ልማት መግባት አለመቻላቸዉ ተገልጾ የካፒታል መጠናቸዉን እንዲያሳዉቁና የካፒታሉን 30% የባንክ ማስታወቂያ እንድታቀርቡ ቢጠየቁም ያላቸዉ የካፒታል መጠን ሳይረጋገጥ ቦታዉ የተፈቀደ መሆኑ፤
- በ2005 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለመስጠት 105 ዕቅድ ተይዞ ክንዉን 39 (37%)ና የስራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች ብዛት 5000 ዕቅድ የተያዘ ሲሆን ክንውን 1,841(36.6%) አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፡
- በ2007 በጀት አመት ለ100 እንዲሁም እስከ 3ኛው ሩብ አመት ደግሞ ለ72 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ36 ፕሮጀክቶች ብቻ ማለትም ከእቅዱ (50.2%) ብቻ የተፈጸመ መሆኑ ልዩ ትኩረት ለሚሹ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ አፈጻጸም ለማስገባት በአመቱ 11 እቅድ ተይዞ እስከ 3ኛው ሩብ አመት 4(36%) ብቻ መከናወኑ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በ2006 በጀት አመት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ልዩ ትኩረት ለሚሹ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ አፈጻጸም ለማስገባት 11 ታቅዶ በአመቱ 3 (27.3%) ብቻ መሆኑ፤
- ከደሴ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት በ2005 በጀት ዓመት ዉስጥ 57 የኢንቨሰትመንት ፍቃዶች መሰረዛቸው፤

**11. ለኢንቨስትመንት በሊዝ የሚሰጡ መሬቶች (ቦታዎች) የሊዝ ገቢ በወቅቱ መሰብሰብ ቢኖርበትም፣**

**ባህር ዳር አገልግሎት ጽ/ቤት**

- ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት በ20/06/2007 የተወሰደዉ መረጃ እንደሚያሳየዉ የኢንቨስትመንት መሬት በሊዝ ከወሰዱ 210 ባለሃብቶች ዉስጥ በውዝፍነት ያልተሰበሰበና ከ2 ዓመት እስከ 10 ዓመት ድረስ ብር 27,396,701.46፣ ከ2 ዓመት በታች ብር 6,823,843.20 በጠቃላይ ብር 34,220,544.66 በሊዝ ከተሸጡ መሬቶች መሰብሰብ ሲገባው እስከ 10 ዓመት በውዝፍነት የታየ መሆኑ፤

**ጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት**

- ከጎንደር ከተማ ክፍለ ከተሞች የኢንቨስትመንት መሬት በሊዝ ከወሰዱ ባለሃብቶች ዉስጥ 24 የሚሆኑት ብር 1,139,082.27 ከ2 እስከ 9 ዓመት ድረስ ለሚሆን ጊዜ ያላስገቡና 74 የሚሆኑት ብር 20,827,171.84 በ2 ዓመት ዉስጥ ሊከፍሉ ሲገባ ያልከፈሉት ያለባቸዉ መሆኑ፤21 የሚሆኑት ባለሃብቶች የሊዝ ዉላቸዉ ለገቢ ሰብሳቢዉ መ/ቤት ያልቀረበ መሆኑና 180 ከሚሆኑት ባለሃብቶች የተሰበሰበና ያልተሰበሰበዉ የሊዝ ክፍያ በግልጽ ማስረጃ የማይታወቅ መሆኑ፤

**ደሴ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት**

- በደሴ ከተማ አስተዳደር የኢንቨስትመንት መሬት በሊዝ ከወሰዱ 142 ባለሃብቶች ዉስጥ 36 የሚሆኑት ብር 2,337,643.70 ከ2 እስከ 8 ዓመት ድረስ ለሚሆን ጊዜ ያልከፈሉና 96 የሚሆኑት ብር 1,493,207.14 በ2 ዓመት ዉስጥ ሊከፍሉ ሲገባ ያልከፈሉት ውዝፍ ያለባቸዉ መሆኑንና 10 የሚሆኑት ያለባቸዉ እዳን በተመለከተ ማስረጃ ያልቀረበባቸዉ መሆኑ የሊዝ ክፍያ በአግባቡ እየተሰበሰበ አለመሆኑን የሚሳይ መሆኑ፤
- በ15/02/05 ዓ.ም ደሴ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ኮሚቴ በማቋቋም በሊዝ ቦታ ወስደዉ በወቅቱ ገንዘብ ያልከፈሉ ባለሃብቶችን ዝርዝር የመለየት ስራ የሰራ ሲሆን ዉዝፍ ያለባቸዉ መሆኑ ከተገለጹት 62 ባለሃብቶች ዉስጥ 3 ዉል ፈጽመዉ ክፍያ ይከፈሉ አይከፈሉ የማይታወቅ እንዲሁም 35ቱ ከ3-5 ዓመትና 12ቱ የ2 ዓመት ዉዝፍ ያለባቸዉ መሆኑና የሊዝ ገቢ ዉዝፍ የመከታተሉና መሰብሰቡ ስራ በቋሚነት የባለሙያ የስራ ድርሻ ሆኖ ሊሰራ ሲገባ በኮሚቴና ወጥነት በሌለዉ አግባብ መሰራቱ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በየግኝቶቹ ላይ አስፈላጊውን የማሻሻያ አስተያየት በዝርዝር ሪፖርታችን አስተላልፈናል፡፡

### 5. የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሌጅ የሰልጣኝ ምልመላ፣መረጣ፣ትምህርትና ስልጠናን እንዲሁም የሃብት አስተዳደርና አጠቃቀምን በተመለከተ፤

12. **ኮሌጁ የሚቀበላቸው ሠልጣኞች የየፕሮግራሙን የመግቢያ መስፈርቶች ያሟሉና ከምልመላና መረጣ ጋር በተያያዘ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት በተደረገበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡**

- አልፎ አልፎ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ሰልጣኞች የሚመለመሉበት ሁኔታ መኖሩ (ለማሳያም አንድ የ23ኛ ዙር የአድማ ብተና ምልምል ፖሊስ ሰልጣኝ በጎንደር ከተማ በ3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ተመልምሎ የመጣ ማንበብና መፃፍ የማይችል ሆኖ በመገኘቱ የተሰናበተበት ሁኔታ መኖሩ፤
- ወደ ኮሌጁ የሚገቡ ዕጩ ፖሊሶችም በአመለካከትም ሆነ በተግባር በሕብረተሰቡም ሆነ በየደረጃው በሚገኙ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ በሚገባ እንዲገመገሙና እንዲተቹ ያለማድረግ፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ ጥፋተኛ መሆናቸው እየታወቀ ከአጠገቡ እንዲርቁ ብቻ ወደስልጠና እንዲሄዱ የማድረግ ሁኔታ (አልፎ አልፎ) መኖሩ፣
- ሰልጣኞች ተመልምለው ወደ ኮሌጁ የሚላኩት አስቀድሞ በታቀደና ቅድመ ዝግጅት ተደርጐበት ሳይሆን በጀት ተገኘ ሲባል ብቻ በአጣዳፊና በአስቸኳይ መሆኑ የኮሌጁ ችግር መሆኑ በጥናት ቢለዩም የተጠቀሱት ችግሮች ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ግንቦት 11/2008 ዓ.ም ድረስ የቀጠሉ መሆኑ፤ በሚሉት ግኝቶች ላይ አስፈላጊውን የማሻሻያ አስተያየት በዝርዝር ሪፖርታችን አስተላለፍናል፡፡

13. **ኮሌጁ የሚሰጣቸው ስልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱና ደረጃውን የተከተሉ ሊሆኑ ሲገባ፣**

- ኮሌጁ የራሱ የሆነ የሰልጣኞች መቀበያ ጊዜ /ፕሮግራሙ ወጥነት የሌለው በመሆኑ በአብዛኛው ሰልጣኞች በተደጋጋሚ በክረምት ወራት ለስልጠና የሚገቡበት ሁኔታ በመኖሩ ሰልጣኞች በዝናብ እየተመቱ የሚሰለጥኑበትና ስልጠናውን በተመቻቸ ሁኔታ እንዳይከታተሉ የሚያደርገብበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ኮሌጁ የተለያዩ ስልጠናዎችን የሚሰጥበት ቦታ በአንድ ጊዜ መያዝ የሚችለው እስከ 800 ሰልጣኝ ብቻ ቢሆንም ከዚህ በላይ የሆነ ቁጥር የተቀበለበት ሁኔታ መኖሩ (ለምሳሌ በ19ኛ ዙር ምልምል ፖሊስ ስልጠና

ከ1978 በላይ ሰልጣኞችን የተቀበለ መሆኑ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በ2008 በጀት ዓመት ከ1980 በላይ ሰልጣኞች በስልጠና ላይ መገኘታቸው፤

- በቁጥር,ሩ ከሚችላው በላይ በመሆኑ በ2007 በጀት ዓመት የመኝታ ክፍሎች ጥበት በመከሰቱ ፍራሽና ትራስ በትውስት በመጠየቅ ስልጠና ለመስጠት የተገደደበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የ2ኛ ዙር መደበኛ ዲፕሎማ ስልጠና ለክልሉ ፖ/ኮሚሽን 80 ዕጩ መኮንኖችን፣ ለክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን 20 ዕጩ መኮንኖችን፣ እንዲሁም ለአጊራባች 2 ክልሎች በድምሩ 10 (ለእንዳንዱ 5 ) ዕጩ መኮንኖችን ከጥቅምት 1/2008 ዓ.ም ጀምሮ ቅበላ ስለሚደረግ ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ ለኮሌጁ የትምህርትና ስልጠና ዋና የስራ ሂደት በደብዳቤ የተገለጸለት ቢሆንም እስከ 5 ወራት መጋቢት 3/2008 ዓ.ም በፊት የገባ ሰልጣኝ አለመኖሩ ኮሌጁ በራሱ እቅድና ፕሮግራም መመራት የማይችለበት አሠራር መኖሩን ያሳያል፡፡
- ከ2008 በጀት ዓመት በፊት በነበሩ ዓመታት በአንድ ክፍል ከ60-132 ሰልጣኝ እንደነበርና አንድ የተግባር አሰልጣኝ ደግሞ ከ120-150 ለሚሆኑ ሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ ከዚያ ወዲህ ግን 480 ሰልጣኝ በአንድ ላይ በመሆን በማይክራፎን የሚማርበት ሁኔታ የተከሰተና መብራት በሚቋረጥበት ወቅትም ትምህርቱ ስለሚቀጥል ትምህርቱን መስማት የማይቻል መሆኑ፤
- በቀን 11/09/08 ዓ.ም በማሰልጠኛ ተቋሙ ከአቅም በላይ የሆነ ሰልጣኝ በመግባቱ ሰልጣኞች መሬት ላይ ፍራሽ ተንጥፎ የተኙበት ሁኔታ ከመኖሩ በተጨማሪ ከ240 በላይ አዲስ ምልምል ፖሊስ ሰልጣኞች የቀድሞው ህጻናት ግቢ እየተባለ ከሚጠራው ከሌላ ግቢ ውስጥ እንዲኖሩና እንዲያድሩ ያስገደደ መሆኑ፤
- ሁሉም መማሪያ ክፍሎች የሰልጣኞች መኝታ ክፍል የሆኑ ሲሆን 50 ሰልጣኞች መኝታ ቦታ ያላገኑ ከመሆኑም በላይ መማሪያ ክፍል ባለመኖሩ ሰልጣኙ በ16 ተከፋፍሎ ዛፍ ስር እና በድንኳን ስር እየተማሩ የተገኙ መሆኑ፤
- የኮሌጁ ክሊኒክ ፈቃድ ሊያወጣ የሚችል ባለሙያ ባለመቅጠሩ ፈቃድ የሌለው ሲሆን ቀላል የሚባሉ የህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶች በኮሌጁ የሌሉ መሆኑ፤
- በ2004 ታይፈስና ታይፎይድ እንዲሁም በ2007 ቼክ ቦክስ (በፊት ላይ የሚታይና ከፍተኛ ትኩሳት ያለው በሽታ) የመሳሰሉ ወረርሽኞች ተከስተው በተለይ ቼክ ቦክስ የተሰኘው ወረርሽኝ እስከ ስልጠናው ማጠናቀቂያ ሊጠፋ ያልቻለበት ሁኔታ መኖሩ፤
- የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን በ2007 በጀት ዓመት አንድ ትልቅ ድንኳን ከክልሉ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን በመዋስ 2249 ለሚሆኑ ነባር የፖሊስ አባላት ለ1 ወር የተሃድሶ ስልጠና የሰጠ ቢሆንም ስልጠናው በኮሌጁ በዕቅድ ተይዞ የተከናወነ ሳይሆን በፖሊስ ኮሚሽን በኩል በድንገት እንዲሰጥ የተወሰነ መሆኑ፣

14. **ለኮሌጁ አገልግሎት የሚገነቡ ማንኛውም ግንባታዎች የተሟላ ዲዛይን ሊዘጋጅላቸው፤ የዲዛይን ደረጃዎችንና መስፈርቶችን (Specifications) ተከትለዉ በተያዘላቸዉ ጊዜና በጀት መሠረት ሊከናወኑ ሲገባ፣ በኮሌጁ የተደረጉ ግንባታዎችን በተመለከተ በተደረገ ኦዲት እንደታየው፤**

- የኮሌጁ የህንፃ ግንባታ ለመስራት በብር 95,000,000.00 ፓን አፍሪካ ኮንስትራክሽን ኢንጅነርስ ኃ/የተ/ የግ/ማህበር የተባለ ስራ ተቋራጭ አሸንፎ ሲሰራ ከቆየ በኋላ የግንባታውን ጠቅላላ 25% እንዳከናወነ ስራውን

ከታህሳስ 7/2003 ዓ.ም ጀምሮ ሲቋረጥ ተቋራጩ ለስራው ስራ ተመጣጣኝ ዋጋ እስከ ብር 23,750,000.00 ብቻ መከፈል ሲገባው ከቅድሚያ ክፍያው ጋር በጠቅላላው ብር 45,000,000.00/ የውሉን 50%/ በመከፈሉ ስራ ላልተሰራበት ብር 21,250,000.00 ተከፍሎት መገኘቱ በማስረጃ በመረጋገጡ፤

- 75% የሆነውን ቀሪ ስራ ለማጠናቀቅ በድጋሜ ጨረታ ሲወጣ የጠቅላላ ግንባታው ዋጋ ከብር 95,000,000.00 ወደ ብር 115,000,000.00 ከፍ ስላደረገው የኮሌጁን የግንባታ ወጭ በብር 20,000,000.00 ከፍ እንዲል ያደረገ ሲሆን በጠቅላላ ኮሌጁን ከሌሎች ተያያዥ ወጭዎች ውጭ ከብር 41,250,000.00 በላይ እንዲያወጣ ያስገደደ በመሆኑ ጉዳዩ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የመውጫ ስብሰባ እስከተደረገበት ህዳር 24/2009 ዓ.ም ድረስ በክስ ላይ ቢሆንም ውሳኔ ያላገኘ መሆኑ፤
- ተቋራጩ በተጠቀሰው ብር 41,250,000.00 በላይ በሆነ ገንዘብ የተከሰሰ ቢሆንም ለግንባታው ይጠቀምባቸው የነበሩና ኮሌጁም እንደመያዣነት ይጠቀምባቸው የነበሩ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ማሽኖች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቁጥር የጠ/ፍ/ቤት መ/ቁ/32621 በቀን 17/10/2005 ዓ.ም ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት ተቋራጩ ተሽከርካሪዎችንና ማሽኖችን ሊወስድ ችሏል፡፡
- የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ማለትም 11/09/2008 ዓ.ም ድረስ ንብረትነታቸው የፓን አፍሪካ ኮንስትራክሽን ኢንጅነርስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆኑ መጠናቸው በውል የማይታወቅ ብረታ ብረቶችና ሌሎች ቀላል ንብረቶች በኮሌጁ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን እነሱም ለፀሀይና ለዝናብ የተጋለጡ በመሆናቸው ከጥቅም ውጭ በመሆን ላይ የሚገኙ መሆናቸው፤
- የግንባታው አካል የሆነ በ2ኛው ስራ ተቋራጭ ሊቀርብ የሚገባው ከብር 800,000.00 በላይ የሚያወጣ ዲዝል ጀነሬተር እና ዩቲሊቲ ኮኔክሽን በውሉ መሠረት በወቅቱ ባለመገዛቱ ገንዘቡ ከክፍያው ላይ ተቀንሶ እንዲቀር የተደረገ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የተጠቀሰው ጀኔሬተር ዋጋ ከብር 1.5 ሚሊዮን በላይ የሚያወጣ ከመሆኑም በላይ ኮሌጁ ያለ ጀነሬተር ስራውን እንዲያከናውን ያስገደደ መሆኑ፣
- የውሃ መዋኛ ገንዳው ጠርዞቹ እየፈረሱ ከመሆኑም በላይ የውስጡ የመዋኛ ስፍራ የተሰራበት ማቴሪያል እየለቀቀና በአቧራ/በጭቃ እየተሸፈነ ያለበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የቤተ መፅሃፍት ህንፃው እየተሰነጠቀ ከመሆኑም በላይ ጣራው ስለሚያፈስ ዝናብ የሚያርፍበት ግድግዳ እየተጎዳ ያለበት ሁኔታ መኖሩ በሚሉት ግኝቶች ላይ እንደየባህሪያቸው እርምጃ በመውሰድ የኮሌጁን የመማር ማስተማር ሂደት የተሳለጠና ብቃት ያለው እንዲሆን ማድረግ እንደሚገባ በዝርዝር ሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

### 6. የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የህግ ታራሚዎች አያያዝ፤አስተዳደር፤የማረምና ማነፅ እንቅስቃሴን በተመለከተ፤

15. **ለታራሚዎች ከተባይ የፀዱ ንጹህ አየርና በቂ የፀሃይ ብርሃን የሚያገኙ የመጠለያና በቂ የመኝታ ቦታ ሊዘጋጅ ላቸው ሲገባ፣**

- **ደሴ ማረሚያ ቤት** በ2001 ዓ.ም የተሰሩ 8 ክፍል የታራሚ ማደሪያ ክፍሎች የተፋፈገና የጸሀይ ብርሃን የማይገባባቸው መሆናቸው፣ከዚህ ጋር በተያያዘም በማረሚያ ቤቱ 16 የአምዕሮ በሽተኛ ታራሚዎች የሚያድሩበት ክፍል የተጣበበ፣ በቀን ብርሃንና የቪንትሌሽን ሲስተም የሌለው መሆኑ፣

**ኮምቦልቻ ማረሚያ ቤት**

- 6*በ6 ካ.ሜትር በሆነ የማደሪያ ክፍል ውስጥ 44 ታራሚዎች የሚያድሩ መሆናቸው ለአንድ ታራሚ ከሚመደበው 1.2 ካ.ሜ በ0.38 ካ.ሜትር ያነሰ መሆኑ፣
- ሁሉም የታራሚዎች ማደሪያ ክፍሎች የጸሃይ ብርሃን የማይገባባቸው፤ የአየር ማናፈሻ (ፋን) የሌላቸውና ለተባይ መራቢያነት የተጋለጡ መሆናቸው፣
- **በቦረና ማረሚያ ቤት** የታራሚዎች ማደሪያ ክፍሎች ለተባይ የተጋለጡ ናቸው፣ 7*በ9 ካሬ ሜር በሆነ ክፍል ውስጥ 69 ታራሚዎች የሚያድሩ መሆናቸው ለአንድ ታራሚ ከሚመደበው ቦታ 1.2 ካ.ሜ ወደ 0.4 ዝቅ ያለ መሆኑ፣
- **ጭልጋ ማረሚያ ቤት-** ታራሚዎች ደረጃውን ባልጠበቀ ሁኔታ በልምድ በማገር እንጨት በተሰሩ አልጋችና ለረጅም ጊዜ ባገለገሉ አሮጌ የማዳበሪያ ፍራሾች ላይ የሚያድሩ መሆናቸው፤

16. **ታራሚዎች የግል ንጽህናቸዉን የሚጠብቁበት ጽዱና በቂ የመጸዳጃና የመታጠቢያ ክፍሎች ሊኖሯቸው ሲገባ፣**

**በደሴ ማረሚያ ቤት**

- በ2001 ዓ.ም ፕሪዝን ፎሎው ሽፕ (Prison fellowship )በተባለ ድርጅት የተገነቡ ባለ 10 ቋት ሻወርና ባለ 30 ቀዳዳ ሽንት ቤት ለ7 አመታት ያለ አገልግሎት የሚገኙ መሆናቸው፣
- በመንግስት የተገነቡ ባለ 4 ቋት ሻዎሮች ለ1500 የህግ ታራሚዎች አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ሲሆን ሻወሮቹ የክፍል መለያያ የሌላቸውና እርስ በእርስ እየተያዩ እንዲታጠቡ የሚያደርጉ ናቸው፡፤

**በኮምቦልቻ ማረሚያ ቤት፤**

- በማረሚያ ቤቱ ለዝርዝር ኦዲት እስከተደረሰበት መጋቢት 28/2008 ዓ.ም **ድረስ** 399 ህግ ታራሚዎች የሚገኙ ሲሆኑ ለእነዚሁ ታራሚዎች 6 መከለያ በር የሌላቸው፣ ለእርስ በርስ እይታ የተጋለጡ የሽንት ቤት ቀዳዳዎችና 2 የገላ መታጠቢያዎች ብቻ መኖራቸው፣ በሌሊት የመጸዳጃ አገልግሎት የሚሰጡ ሽንት ቤቶች የሌላቸው መሆኑ፣
- **ቦረና ማረሚያ ቤት-**የታራሚዎች የመጸዳጃና የገላ መታጠቢያ ክፍሎች ለአጠቃቀም ምቹ ያልሆኑ የንጽህና ጉድለት ያለባቸውና ለአደጋም ስጋት የሆኑ ናቸው፣ በተጨማሪም በሌሊት የመጸዳጃ አገልግሎት የሚሰጡ ሽንት ቤቶች የሌላቸው መሆኑ፣

**ጭልጋ ማረሚያ ቤት**

- በቀይ መስቀል የተሰሩ 17 የሽንት ቤት ቀዳዳዎች ያሉ ቢሆንም በወቅቱ ካለው 813 ታራሚዎች ቁጥር አንጻር በቂ ያልሆኑና የፊት ለፊት በር መዝጊያ የሌላቸው መሆኑ በሚሉትና በሌሎች በዝርዝር ሪፖርቱ በተመለከቱት ግኝቶች ላይ ተገቢውን የማሻሻያ አስተያየት አስተላልፈናል፡፡

7. በክልሉ የህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን መከላከልና የገበያ ዋጋ ማረጋጋትን በተመለከተ፤

**17. ቢሮዉ በነጋዴዎች የሚፈጸም የንግድ ዕቃዎች ክምችት/መደበቅ፣ ባልተፈቀደ ቦታ የማዘዋወርና የማጓጓዝ ተግባር ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ሲገባ፡-**

**በደሴ ከተማ አስተዳደር፤**

- በ2008 ዓ.ም በቧንቧ ዉሃ ክፍለ ከተማ የንግድ ድርጅቶች ላይ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፣ ለአብነት ያህል ለአንድ ዳቦ ጋጋሪ ድርጅት ለ3 ወራት 45 ኩንታል የዳቦ ዱቄት በመዉሰድ ወደ ዳቦነት ሳይቀይር ዱቄቱን የሸጠ እና ሌላ አንድ ነጋዴ ደግሞ የዳቦ ማቡኪያ ሳይኖረዉ ዱቄቱን ወስዶ የሸጠ ሲሆን የክፍለ ከተማዉ ባለሙያዎችም ጉዳዩን በአካል ሳያረጋግጡ ተጨማሪ ዱቄት እንዲያገኙ በደብዳቤ የፈቀዱ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም አንድ የዘይት ቸርቻሪ ነጋዴ ለህብረተሰቡ ማሰራጨት የነበረባቸዉን 800 ሊትር ዘይት በትክክል ለህብረተሰቡ መሰራጨቱን በበር ከበር ጉብኝት ወቅት ድርጅታቸዉን በመክፈት እንዲያሳዩ ሲጠየቁ ድርጅቱን ከፍተዉ ለማሳየት ፍቃደኛ አለመሆናቸዉና ዘይቱም በድርጅቱ ዉስጥ የሌለ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም አንድ ሌላ የዘይት ቸርቻሪ ነጋዴ ለህብረተሰቡ ሊያሰራጩ ከወሰዱት 800 ሊትር ዘይት ዉስጥ 400 ሊትር ዘይት ለህብረተሰቡ ያላሰራጩና ህገወጥ ተግባር ላይ ያዋሉት ቢሆንም በህግ እንዲጠየቁ አለመደረጉ፤
- በ2008 ዓ.ም አንድ የሽርክና ማህበር የዘይት ጅምላና ችርቻሮ ፈቃድ በማዉጣት ከአምባሰል ንግድ ስራዎች ድርጅት 20,000 ሊትር ዘይት በመዉሰድ 4,500 ሊትር ዘይት ለህብረተሰቡ የተሰራጨ ቢሆንም ቀሪዉ 15,500 ሊትር ዘይት ለህብረተሰቡ ተደራሽ አለመሆኑና ማህበሩም በህግ እንዲጠየቅ አለመደረጉ፤
- የከተማ አስተዳደሩ ነጋዴ የሆኑት አንዲት ግለሰብ ከጂንአድ ያገኙትን 4500 ሊትር ዘይት ያለምንም የዘይት ትስስር 4450 ሊትር ዘይት ከዝነው ያስቀመጡና 50 ሊትር ዘይት በህገ ወጥ ስርጭት የዋለ መሆኑ እየታወቀ ሌላ ተጨማሪ 4500 ሊትር ዘይት ከጅንአድ እንዲያገኙ የተፈቀደ መሆኑ፣
- በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በሚገኘው አራዳ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራትና በግለሰብ ዘይት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች ለህብረተሰቡ መዳረስ ሲገባው በድምሩ 23.39 ኩንታል ስኳርና 2,630 ሊትር ዘይት ከትክክለኛ አሰራር ውጭ እየተሰራ ኪራይ ሰብሳቢነት የተስፋፋ መሆኑ፣
- ከሁሉም ዞንና ከተማ አስተዳደሮች ከ2004_2007 ባሉ 4 በጀት ዓመታት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ያለበቂ ምክንያት የንግድ ዕቃዎችን ያከማቹ ድርጅቶች ብዛት 117 የደረሱ መሆኑ፣

**18. ለሰዉ ጤናና ደህንነት አደገኛ የሆኑ ምንጫቸዉ ያልታወቀ፣ የጥራት ደረጃቸዉ የወረደ፣ የተመረዘ፣ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸዉ/ከባዕድ ነገሮች ጋር የተደባለቁ የንግድ ዕቃዎችን ለሽያጭ እንዳይቀርቡ ቁጥጥር ሊደረግባቸዉ ሲገባ፡-**

**በደሴ ከተማ አስተዳደር**

- በ2008 በጀት ዓመት የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸዉ ምርቶች በሱቆች ለተጠቃሚዉ ህብረተሰብ ሽያጭ የሚፈጸም መሆኑ እና ሽያጭ ሲፈጽሙ በተገኙት ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣ ለአብነት ያህል ሱፐርቪዥን ሲደረግ

97.5 ሊትር ኮካ፣ ፋንታ፣ ስፐራይት፣1 ሊትር ራኒ ጁስ እና 4 ፓኮ ሴሪፋም (የህጻናት ምግብ) የመጠቀሚያ ጊዜ አልፎባቸው በሳላይሽ ፣አራዳ፣ ፒያሳ፣ሰኞ፣ አገር ግዛት፣ ሆጤ እና ቧንቧ ዉሃ ክፍለ ከተሞች መገኘታቸው፣

- በ2008 ዓ.ም ህጋዊ የንግድ ፈቃድ የሌላቸዉ የጎዳና ላይ ነጋዴዎች ባዕድ ነገር የተቀላቀለበት ሽቶ ለህብረተሰቡ የሸጡ መሆኑ እንዲሁም ጎዳና ላይ ከሚነግዱ ህገወጥ ነጋዴዎች ባዕድ ነገር የተቀላቀለበት 550 የሚደርሱ የተለያዩ ዓይነት ሽቶዎች የተገኘ መሆኑ፤
- በ2006 በጀት ዓመት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው 1,401 የተለያዩ የታሸጉ መጠጦች፣ የህጻናት ወተት የታሸገ ጁስ እና ሽኖ ለጋ ቅቤ ለህብረተሰቡ ገበያ ላይ ቀርቦ የተገኘ መሆኑ፣

**በሰሜን ጎንደር ዞን**

- በ2008 ዓ.ም በምዕራብ በለሳ ወረዳ 4 ኩንታል ባዕድ ነገር የተቀላቀለበት ጌሾ መሳይ ነገር የተያዘ ቢሆንም በዘመናዊ መመርመሪያ መሳሪያ ማረጋገጥ ስላልተቻለ ህገወጥ ስራ በሰሩ ግለሰቦች ላይ በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፤ ከሁሉም ዞንና ከተማ አስተዳደሮች ከ2004_2007 ባሉ 4 በጀት ዓመታት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ከምርት ጋር ባዕድ ነገሮችን ቀላቅለዉ የሸጡ ነጋዴዎች/ድርጅቶች ብዛት 2,030 የደረሱ መሆኑ፣

8. **የክልሉ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት አሠጣጥ በተመለከተ፤**

**ዳኞች በውሣኔ ጥራት የሚለኩበት የአሠራር ስርዓትን በተመለከተ፣**

**19. ዳኞች በሚሰጡት የውሣኔ ጥራት መሠረት የሚለኩበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ሲገባ፤**

- በክልሉ በይግባኝ ቀርበው የሚሻሩ፣ የሚሻሻሉ እና ወደ ስር ፍርድ ቤት የሚመለሱትን መዛግብት ከ2003-2007 ዓ.ም የ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ከሚታየው የአፈፃፀም መነሻ 24% የሚሻሩና የሚሻሻሉ የይግባኝ መዛግብት 6% ብቻ ይሆናሉ በሚል የታቀደ ቢሆንም አፈፃፀሙ ሲታይ፡
  - **በይግባኝ** ከቀረቡት የተሻሩ፣ የተሻሻሉና ወደ ስር ፍርድ ቤት የተመለሱት ከአቅርቦት ጋር ሲነፃፀር ከ27.7%- 35% እንዲሁም ውሳኔ ከተሰጣቸው ጋር ሲነፃፀር 30.4%- 42% መሆኑ፣
  - **ለሠበር** ከቀረቡት የተሻሩ፣ የተሻሻሉና ወደ ስር ፍርድ ቤት የተመለሱት ከአቅርቦት ጋር ሲነፃፀሩ ከ12.4%- 41.5% እንዲሁም ውሳኔ ከተሰጣቸው ጋር ሲነፃፀር 16.8%-52.7% መሆኑ፣

**በሰሜን ጎንደር ዞን፤**

- ውሣኔ በብዛት የሚሻርባቸው ወረዳዎች እንዳሉ በ2006 ዓመታዊ ሪፖርት የተገለጸ ቢሆንም የተሻሩበትና ችግሩ የተከሰተበት ምክንያት በየመዝገቡና በየዳኛው አለመለየቱ፣
- የዳኞች አቅም ማነስ፣ በዘመድ አዝማድ መስራትና የሀሰት ማስረጃ መቅረብ በመኖሩ የስራ ጥራት (የፍርድ መዛባት) ችግር እያስከተለ ስለመሆኑ መገለፁ፣
- የይግባኝ መዛግብት መብዛት የተከሰተው ከጥራት ጋር በተያያዘ መሆኑ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ መገለጹ፣
- በመተማ ወረዳ ፍ/ቤት በአንድ መዝገብ በአንድ ችሎት 4 ትዕዛዝ (እግድ) በመተላለፉ ፖሊስ ለአፈጻጸም እንደተቸገረ የገለጸ መሆኑ፣
- በአንዳንድ የወረዳ ፍ/ቤቶች ለጉዳዮች ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ በውሣኔው ቅር የተሰኘ ይግባኝ ሲጠይቅ

የተወሰነዉ ውሣኔ እንደፍርዱ ካልተፈጸመ አንሰጥም እንደሚሉ በ2003 በጀት ዓመት ሪፖርት የተገለጸ ቢሆንም ችግር ያለባቸዉ ወረዳዎች የተለዩበት አግባብ አለመኖሩ፣

- **ለደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍ/ቤት** ለብቻ ሲታይ በ2005 የወንጀል እና በ2006 የፍትሃብሔርና የወንጀል ዳኝነት ይግባኝ ቀርበው ውሣኔ ከተሰጣቸው መዛግብት ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው 41.2% እና 36.9% የተሻሩ፣ የተሻሻሉና ወደ ስር ፍርድ ቤት የተመለሱ መሆኑ፣

**በዳኝነት አገልግሎት የደንበኞች እርካታ የተለካ እምነት የሚጣልበት መሆኑን በተመለከተ፣**

**20. የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ በደንበኞች እርካታ እየተለካ አመኔታ የሚጣልበት ሊሆን ሲገባ፡፡**

**በሠሜን ጎንደር ዞን፤**

- በዳኞችና በባለጉዳዮች መካከል ያሉ ደላላዎችን በመለየት ችግሩን በሚፈታ ደረጃ የእርምት እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑ፣
- በ2003 እና 2005 ዓ.ም ከፍተኛው ፍ/ቤት ላይ እና በ2006 ዓ.ም በ14 ወረዳ ፍ/ቤቶች ላይ የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት የተደረገ ሲሆን የአገልግሎት አሠጣጡ ችግሮች በየዓመቱ በተደጋጋሚ የሚከሰቱመሆኑ፤
- የባለጉዳዮች መዝገብ ሲቀጠር አገልግሎት የሚያገኙበት ሠዓት በግልጽ አለመቀመጡ፣ የዳኞች ትዕዛዝ ከተፈጸመ በኋላ ተጨማሪ ትዕዛዝ መስጠት፣
- በዞኑ ከ2003-2006 ዓ.ም ተከሳሽ ባለመቅረብ 1350 እና ምስክር ባለመቅረብ 580 በድምሩ 1930 የወንጀል መዛግብት የተዘጉ መሆኑ፣

**ደቡብ ወሎ ዞን፤**

- በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ደንበኞች ጉዳያቸው የሚቀርብበት ችሎት ስለማይገለጽ አንዳንድ ባለጉዳዮች በቀጠሮው ቀን ደሴ በመምጣት ሙሉ ቀን ሲጠባበቁ ከዋሉ በኋላ ባለመጠራታቸው ቅሬታ ሲያቀርቡ ወደ ተዘዋዋሪ ችሎት እንደሄደ የሚነገራቸው መሆኑ፣
- ከከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሚላኩ የእግድ ትዕዛዞች የወረዳ ፍርድ ቤቱን የመዝገብ ቁጥር የማይጠቅስ መሆኑ፣
- ከወረዳ ፍርድ ቤቶች ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚመጡ ውሣኔዎች የማይነበቡና ማኅተም የማይደረግባቸው በመሆኑ ባለጉዳዮች እስከ 200 ኪሎ ሜትር ተመልሰው ሄደው አስተካክለው እንዲመጡ የሚደረግ ሲሆን ከፍትሃብሔር ዳኝነት ለመገለጫ ያህል 21 መዛግብት መኖራቸው፣
- የመዝገብ ቁጥር 02-09134 በቸልተኝነት በተሽከርካሪ ሠው ገጭቶ መግደል ተከሳሽ ባለመቅረቡ በ2 ቀጠሮ መዘጋቱ፣

**ምዕራብ ጎጃም ዞንና ወረዳዎች፤**

- በቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ለ23/10/2006 ዓ.ም ቀጠሮ ተሰጥቶ ከምስክሮች ጋር 5 ሠዎች ቡሬ ከመጡ በኋላ አገልግሎት ሳያገኙ በመዋላቸው ቅሬታ ሲያቀርቡ መዝገቡ ወደ ቁጭ ተዘዋዋሪ ችሎት እንደሄደ መነገሩ፣
- ቡሬ ወረዳ ባለጉዳዮች ለአገልግሎት አስተዳደርና ቅሬታ ሰሚ ክፍል ቅሬታ በማቅረባቸው ከመዝገብ ጋር የተገናኙ 7 ቅሬታዎች ወደ ሰብሳቢው ዳኛ የተመሩ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም የተሰጣቸው መፍትሄ ያልታወቀ መሆኑ፣

መዛግብት በወቅቱ የዳኝነት ውሣኔ የሚያገኙ ስለመሆኑ፣

21. የዳኝነት ውሣኔዎች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ውሳኔ አግኝተው ሊጠናቀቁ ሲገባ፡

- ከ2003-2007 በጀት ዓመት የ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት በክልሉ ከሚቀርቡ ጉዳዮች ሁሉም መዛግብት ከ60 ቀናት በታች እድሜ ውስጥ ይጠናቀቃሉ ቢባልም በፍርድ ቤቱ ረዥም እድሜ ካላቸው መዛግብት ውስጥ በናሙና የተመረጡት ዝርዝር ኦዲት ሲደረጉ፡
  - ➢ አንዳንድ መዛግብት ለምርመራ የተቀጠሩ ቢሆንም አልተመረመሩም በሚል በተከታታይ እስከ 16 ጊዜ ለምርመራ የሚቀጠሩ መሆኑ፣
  - ➢ ለምርመራ እየተቀጠሩ ባለመመርመራቸው በተከታታይ እና በተደጋጋሚ ተለዋጭ ቀጠሮ በመሠጠቱ ምክንያት ብቻ መዛግብት ካላቸው ዕድሜ ላይ እስከ 3 ዓመት ተጨማሪ ዕድሜ እንዲኖራቸው ማድረጉ፣
  - ➢ ለምርመራ ከተቀጠሩ የባለጉዳዮች መዛግብት ውስጥ ሳይመረመሩ ተለዋጭ ቀጠሮ የሚሰጣቸው በርካታ ሲሆኑ ከ60 መዛግብት 30 (50%) ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚሸፍን መሆኑ፣

**ሠ/ጎንድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

- የመዝገብ ቁጥር 02-07053 በውንብድና ሙከራ ወንጀል ክስ ቀጠሮ ከ24/9/03 ዓ.ም ጀምሮ ደባርቅ ተዘዋዋሪ ችሎት በነፃ እስከተወሰነበት 26/3/07 ዓ.ም ድረስ ለ3 ዓመት ተከሉ 25 ጊዜ ቀጠሮ መሰጠቱ፣
- የመዝገብ ቁጥር 02-15550 በከባድ የሠው ግድያ ወንጀል በ15/5/06 ዓ.ም ክስ ለመስማት የተቀጠረ ቢሆንም በማረሚያ ቤት ችግር ያልቀረበ ሲሆን እስከ 23/4/07 ዓ.ም ድረስ 11 ጊዜ ቀጠሮ የተሰጠ ከመሆኑም በተጨማሪ በ25/7/06 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለ28/9/06 ዓ.ም በመቀጠሩ ለአንድ ቀጠሮ 62 ቀናት መሰጠቱ፣
- መዝገብ 01-21257 ከጭልጋ ወረዳ ለከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ ሲቀርብ በዳኛ ችግር ምክንያት በ4 ቀጠሮ 135 ቀናት እንዲዘገይ መደረጉ፣
- መዝገብ 01-13742 ከተከፈተ 20/02/05 እስከ 14/4/07 ዓ.ም ድረስ 30 ጊዜ የተቀጠረ እንዲሁም ለምርመራ እየተባለ 3 ጊዜ ቀጠሮ የተሰጠውና በኦዲት ወቅትም በቀጠሮ ላይ የነበረ መሆኑ፣

**ደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍ/ቤት፣**

- የደሴ ከተማ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ፍሬ ነገሩ ላይ ተመስርቶ ባለመሆኑ ወደ ፍሬ ነገሩ ገብቶ እንዲያከራክር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መዝገቡ ወደ ወረዳ ፍ/ቤቱ ተመልሶ መታየት ከጀመረበት ከ20/9/06 -18/6/07 ዓ.ም በ9 ወራት ውስጥ ለ30 ጊዜ ቀጠሮ መሰጠቱ፣
- በጠቅላይ ፍርድ ቤት ረዥም እድሜ ካላቸው መካከል በናሙና ዝርዝር ኦዲት ሲደረግ የሚጠናቀቁበት የጊዜ ግምት 3 ወራት ቢሆንም፡

➢ በቀጠሮዎች መካከል ያለው ርዝመት በአማካኝ 15 ቀናት ሊወስድ እንደሚችል ከ2003-2007 የ5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ላይ ቢመለከትም የቀጠሮ ጊዜ ርዝመት እስከ 90 ቀናት ድረስ በማርዘም ቀጠሮ ይሰጣል፤ እስከ 68 ወራት እድሜ ያስቆጠሩ መዛግብት መኖራቸው፣

- በጠቅላይ ፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 01-31950 ጎንደር ተዘዋዋሪ ችሎት በ27/06/07 ዓ.ም የሄደ ቢሆንም አልተመረመረም በማለት ከ81 ቀናት በኋላ እንዲቀርብ ለ19/09/07 ዓ.ም መቀጠሩ በሚሉትና በሌሎችም ግኝቶች ላይ አስፈላጊውን የማሻሻያ አስተያየቶች በዝርዝር አስገንዝበናል፡፡

**የተከበሩ አቶ ይርሳው ታምሬ!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ በክዋኔ ኦዲት ላይ የተደረገውን የክትትል ኦዲት ሪፖርቶችን አቀርባለሁ፡፡**

1. **የክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን፤**

22. **በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሠረት ማስተካከያ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች፤**

**ደሴ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት፤**

- በመኪና እቃዎች መለዋወጫ ንግድ የተሰማሩ የደሴ ከተ/አስ/ገ/ጽ/ቤት ግብር ከፋይ የ2003 የግብር ዘመን ሂሳባቸው ተመርምሮ ብር 560,410.21 ግብር የሚከፈልበት ገቢ እንዳገኙ ቢረጋገጥም፤የክትትል ኦዲቱ እስከ ሚጠናቀቅ ታህሳስ/2009 ድረስም ያልተወሰነና ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

**ጎንደር ከተማ አስተዳደር ገቢወች ጽ/ቤት፤**

- አንድ የቡና ጅምላ ንግድ የተሰማሩ ግብር ከፋይ የ2002 ግብር ዘመን ሂሳብ መዝገባቸው ተመርምሮ የኦዲት ሪፖርቱ በቀን 30-04-04 ዓ.ም ለአወሳሰን የተላከ ቢሆንም የግብር ውሳኔ ከአንድ አመት በላይ በዘገየበት በቀን 06-06-05 ዓ.ም ግብር፤ታክስና ቅጣት በድምሩ ብር 600,954.10 የተወሰነባቸው ሲሆን በቀን 08-06-05 ዓ.ም የግብር ውሳኔው ለግብር ከፋዩ የተሰጠ ቢሆንም ክፍያ ያልፈጸሙ/ ይግባኝ ያልጠየቁ መሆኑ፤ በ2004 የ5 ወራት እንዲሁም እስከ ጥር መቅረብ ከሚገባቸው የ2005 የግብር ዘመን ውስጥ የ6 ወራት የቫት ሪፖርቶች ፋይላቸው ውስጥ አለመገኘታቸው፤

**ጎንደር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት**

- አንድ በላኪነት ንግድ የተሰማሩ ግብር ከፋይ የ2001 ግብር ዘመን ብር 177,847.85 ግብርና መቀጫ የተጣለባቸው ሲሆን በቀን 30-02-04 ዓ.ም 50% ከፍለው ይግባኝ የጠየቁ ቢሆንም ቀሪ ክፍያውን እስከ ሚያዚያ 2004 አጋማሽ ድረስ ያልከፈሉ መሆኑና፤ በቀን 18/05/04 ዓ.ም የ2002 ቀሪ ግብርና ቅጣት ብር 57,283.68 ለግብር ከፋዩ የግብር ውሳኔው የደረሰው ቢሆንም፤ክፍያ ስለመፈጸሙ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ፋይሉ ጋር ያልተያያዘ መሆኑ፣
- አንድ በህንፃ መሣሪያ የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ የደሴ ከተ/አስ/ገ/ጽ/ቤት ግብር ከፋይ፤ ከንግድ ዘርፋቸው ውጭ በተለያዩ ወራቶች በድምሩ ብር 730,397.75 የፍራሽ ግዥ በወጪ የተያዘላቸው መሆኑ፣

**ደሴ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት**

- በየግብር ዘመኑ በተለያዩ የግብርና ታክስ ማጭበርበር ወንጀሎች ክስ ሊመሰረትባቸውና ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ በርካታ ግብር ከፋዮች በክልሉ ገቢዎች ባለስልጣንና በከተማ አስተዳደሩ ትእዛዝ መሰረት በይቅርታ የሚታለፉና ክሳቸው እንዲነሳ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩ፤

- የደሴ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ግብር ከፋይ የሆኑት አንድ ባለሆስፒታል በ22/09/03 ዓ.ም በጽ/ቤቱ ባለሙያዎች በሆስፒታላቸው ውስጥ በተደረገ ፍተሻ 11,536 ታካሚዎች የውስጥ መዝገባቸው ላይ የተመለከቱ ቢሆንም፤ ከእነዚህ ታካሚዎች ውስጥ ለ5,356 (46.4%) ብቻ የክፍያ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው መገኘቱ፣

**በክልል ደረጃ የቀን ገቢ ጥናትን በተመለከተ፤**

- የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዮች የሚጠናው የቀን ገቢ ግምት በመመሪያ መሰረት በ3 የተለያዩ ደረጃዎች መጠናት ቢኖርበትም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚጠና፤አግባብነት ያላቸው በቂ መረጃወች ግምት ውስጥ የማይገቡ፤ ግብር የሚከፈልበት አመት ካለቀ በኋላ እየተጠና ለግብር ውሳኔ የሚውል መሆኑ፤ በከተማው ውስጥ አሉ በሚል በመረጃ የተያዙ የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዮችም በሙሉ የማይጠኑ መሆኑ፤

**ጎንደር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት፤**

- የጎንደር ከተ/አስ/ገ/ጽ/ቤት ግብር ከፋይ የሆነ አንድ ሆቴል የ2001 የግብር ዘመን በግብር ከፋዩ የቀረበ የሂሳብ መዝገብ ውድቅ ሲደረግ፤ ግብሩን ለመወሰን የቀን ገቢ ጥናቱ በቀን 01/02/04 ዓ.ም ተጠንቶ የቀረበ መሆኑ፣ ግብር ከፋይ የ2002 እና 2003 የግብር ዘመናት ግብርና ታክስ የቅጣት ማቅለያ ቅፅ ሞልተው ያቀረቡ ቢሆንም፤የግብር ውሳኔ ማሳወቂያ ቅፁ እና የተጠቀሱትን 2 ዓመታት ግብር ስለመክፈላቸው የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ፋይላቸው ላይ አለመገኘቱ፣ በ2003 የ2 ወራት፤ በ2004 የ7 ወራት በ2005 የ6 ወራት የቫት ሪፖርቶች ፋይላቸው ላይ ያልተገኘ መሆኑ፤

**ደሴ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት፤**

- አንድ የደሴ ከተ/አስ/ገ/ጽ/ቤት ግብር ከፋይ "የግብርና ታክስ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቁጥር 114/90 በቀን 15/05/93 ዓ.ም በሰጠው ብያኔ በደሴ ከተማ ቀበሌ 10 የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 858 የሆነ የመኖሪያ ቤት ጽ/ቤቱ እንዲያስተዳድር የወሰነ ቢሆንም፤ የተጠቀሰው ቤት በኤግዚት ስትራቴጅ ተለቀልኛል በሚል በግለሰቡ ስም ዞሮ እየተጠቀሙበት እንደሚገኝና የመንግስት ንብረት በህገ ወጥ መንገድ እንዴት ወደ ግለሰብ እጅ ሊዛወር እንደቻለ ዝርዝር መረጃ እንዲላክለት የደሴ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት በቁጥር 05/9819/03 በቀን 02/10/03 ዓ.ም ለቀበሌው የፃፈ ቢሆንም ምላሽ ያላገኘና በኦዲቱ ወቅት እንደተረጋገጠው ግለሰቡ የመንግስትን ንብረት ያለአግባብ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ታውቋል፡፡
- አንድ በህንፃ መሳሪያ ንግድ የተሰማሩ የደሴ ከተ/አስ/ገ/ጽ/ቤት ግብር ከፋይ የሚፈለግባቸው ግብር፣ታክስና ቅጣት ብር 948,497.20 ጽ/ቤቱ የወሰነባቸው ሲሆን፤አስፈቅደው ካሳተሙት ደረሰኝ ውጭ በድጋሚ ተመሳሳዩን ደረሰኝ በማሳተም በህገ ወጥ መንገድ ተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰብሰባቸውና ገቢያቸውን በመደበቃቸው የደቡብ ወሎ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በ25/07/04 ዓ.ም በዋለው ችሎት 15 ዓመት ከ3 ወር እስራትና ብር 191,400.00 የገንዘብ ቅጣት በሌለበት ቢቀጡም ግለሰቡ በመጥፋቱ ምክንያት ፍርዱ ተፈፃሚ ሊሆን አልቻለም፡፡
- አንደ ባለ ዳቦ ቤት የሆነ ግብር ከፋይ ለ2003 የግብር ዘመን ራሳቸው በሰጡትና በፊርማቸው ባረጋገጡት የቀን ገቢ ግምት ብር 19,810.00 መሰረት ግብር ተወስኖ ቢሰጣቸውም ቅሬታ በማቅረባቸው፤በቀን 02/09/04 ዓ.ም የጽ/ቤቱ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ግብር ከፋዩ ያቀረቡት ቅሬታ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ይሁን እንጅ በወቅቱ የጽ/ቤቱ ሃላፊ የኮሚቴውን ውሳኔ አጽድቀውት የነበረ ቢሆንም፤ ከረጅም ወራት ቆይታ በኋላ በቀን

10/02/05 ዓ.ም ብር 304,258.75 ግብር እንዲከፍሉ የተወሰነበትን ሃሳብ ሽረው፤ግብር ከፋዩ በተያዘላቸው ቅድሚያ ግብር ክፍያ (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብር 67,400.38 ስሌት መሰረት ብር 101,576.08 እንዲከፍሉ ወስነዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ብር 202,682.67 ግብር ሳይከፍል ከመቅረቱም በተጨማሪ ውሳኔው ግብር ከፋዩ ከወሎ ዩኒቨርስቲ ጋር በቀን 16/02/03 ዓ.ም ካደረጉት የዳቦ ሽያጭ ውል በፊት ያሉትን የግብር ዘመኑን 3.5 ወራት ያላካተተ እንደሆነ ታውቋል፡፡ ግብር ከፋዩም ዝቅ ተደርጎ በተወሰነላቸው ግብር መጠን ላይ እንደገና 50% በመክፈል ይግባኝ የጠየቁ መሆኑ ቢታወቅም በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡

**ግብርና ታክሱ ተወስኖ እያለ ገቢው አለመሰብሰብን በተመለከተ፤**

23. **በሂሳብ መዝገብም ሆነ በቀን ገቢ ግምት ጥናት ወይም በመረጃ መሠረት የገቢ ግብር ሂሳብ ተጠንቶ/ ተሰልቶ በህጉ መሠረት ግብር እንደተወሰነ ግብር ከፋዩ እንዲያውቀው ተደርጎ የመንግስት ገቢ በወቅቱ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ይሁንና፤**

**በደሴ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት፤**

- አንድ በጽህፈት መሳሪያ የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ የደሴ ከተ/አስ/ገ/ጽ/ቤት ግብር ከፋይ የንግድ ፈቃዳቸውን መመለስ እንደሚፈልጉ ለጽ/ቤቱ ባመለከቱት መሰረት የ2002 በጀት ዓመት የታክስ ኦዲት ምርመራ ተደርጎላቸው ብር 1,958,908.10 ግብርና ታክስ ቢወስንባቸውና ላቀረቡት ቅሬታም በ09/09/04 ዓ.ም ተቀባይነት እንደሌለውና ግብራቸውን መክፈል እንዳለባቸው አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ቢወስንም፤ ግብር ከፋዩ ይግባኝ ያልጠየቁና የንግድ ፈቃዳቸውን ያልመለሱ ሲሆን፤ የመንግስት ከፍተኛ መጠን ያለው ግብርና ታክስም በወቅቱ ሳይሰበሰብ ተንጠልጥሎ ያለና ጽ/ቤቱም ቀጣይ እርምጃዎችን ያልተወሰደ መሆኑ፣ በሚሉት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ ቀደም ሲል በመደበኛ ዝርዝር ኦዲቱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

## 2. እንጅባራ ከተማ አገልግሎት ጽህፈት ቤት

### 24. በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሠረት ማስተካከያ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች

- አንዲት የከተማው ነዋሪ ቀደም ሲል በይዞታ ቦታዋ ላይ መንገድ ስለወጣባት ለይዞታ ቦታዋ ትክ 10×20=200 ካ/ሜ. የድርጅት ቦታ በከንቲባ ኮሚቴ ተወስኖ እንዲሰጣት ቢደረግም ቦታውን ለማስረከብ በሚኬድበት ወቅት ሌላዋ የከተማ ነዋሪ ግለሰብ ካሣ ባልተከፈለኝ የይዞታ መሬት ላይ አላስለካም በማለቷና በተደጋጋሚም አምባጓሮና ሁከት እየፈጠረች ስላስቸገረች ቦታውን ለግለሰቧ ለክቶ ማስረከብ አለመቻሉ፤ ግለሰቧም በተደጋጋሚ አቤቱታ በማቅረብ እየተጉላላች የምትገኝና ቦታውም ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤
- የዘንገና ኮሌጅ ከተሰጠው ቦታ 6 ሜትር ከኮሌጁ በስተምዕራብ አቅጣጫ ወጥቶ ሲያጥር ግንባታው ደግሞ በዚሁ አቅጣጫ ከ3 ሜትር ያላነሰ ወደ መንገዱ ገብቶ በመገንባቱ በኮሌጁና ከኮሌጁ በስተሰሜን በኩል ካለው አንድ ብሎክ መንደር መካከል በሚገኘው 8 ሜትር ስፋት ባለው መንገድ ላይ የመጣበብ ችግር መፍጠሩ፣
- አገልግሎት ጽ/ቤቱ በቁጥር እ/አገ/2090/85/2001 በቀን 3/4/2001 እና በቁጥር እ/አገ/4079/85/2001 በቀን 16/4/2001 በፃፋቸው ደብዳቤዎች ላይ አንድ የከተማው ነዋሪ ከድርጅት ቤታቸው ፊት ለፊት ከተፈቀደላቸው ፕላን ውጭ ግንባታ እየገነቡ መሆኑ በአካል መረጋገጡ፣

- የከተማው ነዋሪዎች ካስፀደቁት ፕላንና ከተፈቀደላቸው የግንባታ ዲዛይን ውጭ የተለያዩ ግንባታዎችን ገንብተው የተገኙ ሲሆን እንዲያፈርሱ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ፈቃደኛ ሊሆኑ አለመቻላቸውና እርምጃ ሳይወሰድ የሚገኝ መሆኑ፣
- በተጨማሪም አንድ ግለሰብ ከተፈቀደ ፕላን ውጭ ያለአግባብ ሕገ-ወጥ ግንባታ መገንባታቸው፣ ሌሎች ግለሰቦች በብሎኬት ለመሥራት ፕላን አሠርተው በጭቃ መሥራታቸው እንዲሁም አንድ ሌላ ግለሰብ በቀበሌ 01 የተሰጣቸው ቦታ ካርታና ፕላኑ 425 (17×25) ካ/ሜ ሲሆን ቦታው ሲለካ 725 (29×25) ካ/ሜ በልዩነት 300 ካ/ሜ ቦታ አላግባብ መያዛቸውና ለሕዝቡ አገልግሎት የሚሰጠውን የውኃ ቦኖ ጨምረው ከልለው ማጠራቸው፣
- በከተማዋ ውስጥ የኢንቨስትመንት ቦታ ወስደው ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ያላደረጉ፣ ግንባታ ጀምረው ለረጅም ጊዜ ያቋረጡ እና የግንባታ ሥራቸውን በውሉ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ መሰረት ያላጠናቀቁና አገ/ጽ/ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት በፃፋቸው ደብዳቤዎች ላይ የተገለፁ በርካታ ባለሃብቶች መኖራቸው፤
- በተጨማሪም በከተማው 01 ቀበሌ 5 ባለሃብቶች የኢንቨትመንት ቦታ ተረክበው ጂ+3 ዲዛይን ያስፀደቁ ቢሆንም ለረጅም ጊዜ ግንባታ አለመጀመራቸው፣
- አገ/ጽ/ቤቱ በቁጥር እ/አገ/9025/101/2002 በቀን 02/04/2002 በፃፈው ደብዳቤ ላይ በከተማው አንድ ባለሃብት ለኢንቨትመንት አገልግሎት የሚውል 2000 ካ/ሜ ቦታ ተፈቅዶላቸው ጂ+3 የሆነ ዲዛይን ያስፀደቁ ቢሆንም ምንም ዓይነት የግንባታ እንቅስቃሴ አለመጀመራቸውን በመጥቀስ ይህ ማስጠንቀቂያ በደረሰ በ10 ቀናት ውስጥም የግንባታ ማቴሪያል በቦታው በማቅረብ የግንባታ ሥራ እንዲጀምሩ፤ የማይጀምሩ ከሆነ ቦታውን እንደሚነጥቅ ያስጠነቀቀ ሲሆን ይህ ኦዲት እስከተጠናቀ ድረስ የግንባታ ሥራው እንዳልተጀመረ መገለፁ፣
- በ2001 ዓ.ም. አንድ የጽ/ቤቱ ባለሙያ ለአንዲት የከተማው ነዋሪ 280 ካ/ሜ. ቦታ ለክቶ ሲያስረክብ በ1989 ዓ.ም ሌላ አንደ የከተማ ነዋሪ ተመርተውት ከነበረው 1100 ካ/ሜ የድርጅት ቦታ ውስጥ 160 ካሬ ሜትሩን በድጋሚ በመለካት ለግለሰቧ ማስረከቡ፣
- በሁለት ግለሰቦች መካከል ያለን አንድ የከተማ ቦታ በተመለከተ አገ/ጽ/ቤቱና ሌላ አንድ የከተማ ነዋሪ እየተከራከሩበት ባለበት ሁኔታ ሌሎች ሁለት ግለሰቦች ከተሰጣቸው ካርታና ቦታ ውጭ በገዛ ፈቃዳቸው ቦታውን አስፋፍተው ሲያጥሩ በመገኘታቸው አገ/ጽቤቱና ቀበሌ ለማስቆም በተደጋጋሚ ጥረት ቢያደርጉም እምቢተኛ ከመሆናቸውም በላይ የአገ/ጽ/ቤቱ ሙያተኞች የወሰን ችካል ለማስቀመጥ በመሣሪያ ሲለኩ የተቸከለውን ችካል ነቅለው በመጣል አናስለካም ማለታቸው እና ቦታውን በድንጋይ ክምችት በመዝጋት ሌሎችን ግለሰቦች መውጫና መግቢያ ማሳጣታቸው መገለፁ፣
- ከተማው አንድ ባለሃብት ለጣውላ መሰንጠቂያ ከተፈቀደላቸው 11,200 ካ/ሜ. የድርጅት ቦታ በተጨማሪ 1750 ካ/ሜ. ቦታ አስፋፍተው ያለአግባብ አጥረው መያዛቸው፣ (በክትትል ኦዲቱ ወቅት 1750 ካ/ሜ የተመለሰ ቢሆንም 11200 ካ/ሜ ያለስራ ታጥሮ የተቀመጠ መሆኑ ታውቋል)፤
- በከተማው 01 ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ አንዲት ግለሰብ በቦታው ላይ መገንባት ያለበት ጂ+3 እና በላይ እንጅ ከዚህ በታች መገንባት እንደማይፈቀድ ቢነገራቸውም ተገዥ ባለመሆን፣ሕጋዊ ፕላን አሠርተው በሚመለከተው መ/ቤት ሳያስፀድቁ እና የግንባታ ፈቃድ ሳያወጡ ጨለማን ተገን በማድረግ የራሳቸውን ግንባታ እየገነቡ የሚገኙ መሆኑ መገለፁ፣ (በቦታው አሁንም ያለው ግንባታ ከፕላኑ ውጭ ጂ+0 ነው)፤

- በከተማዋ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ድልድዮች ደረጃቸውን የጠበቁና ምቹ አለመሆናቸው፣ ለአብነትም ዳሽን ባንክ ጀርባ የሚገኘው የምስኪ ወንዝ ድልድይ ከእንጨት የተሠራ ሆኖ ወንዙ ሲሞላ በድልድዩ በላዩ ላይ ስለሚፈስ ድልድዩ ወደ አንድ በኩል ያጋደለ (ያዘነበለ) መሆኑና መንገደኞችን ስጋት ላይ የጣለ መሆኑ፣
- በከተማው ውስጥ እንስሳትን የሚያረቡ ግለሰቦች፣ሆቴሎችና ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ከቤታቸው የሚወጣውን የደረቅና ፋሳሽ ቆሻሻ የሚጥሉት መኖሪያ ቤታቸው/ድርጅታቸው አካባቢ፣መንገድ ዳር እና በአካባቢያቸው በሚገኝ ቦይ ውስጥ መሆኑ፤ይህንም የሚከላከል የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ስራ አለመኖሩ፣
- የከተማ ቦታ ባለይዞታዎችን በተመለከተ ሙሉና የተጠናከረ መረጃ ባለመኖሩ ግለሳቦቹ በወቅቱ መክፈል የሚገባቸውን የአፈርና የጣሪያ ግብር የማይከፍሉ መሆኑ፤የሚከፍሉትም ለመሸጥ ወይም ለማዛወር ወደ አገ/ጽ/ቤቱ ሲመጡ ብቻ መሆኑ እና ተገቢው ጥቅም በወቅቱ ባለመሰብሰቡ ምክንያት የከተማዋን ዕድገት እያጓተተው የሚገኝ መሆኑ፣
- ከይዞታቸው በመፈናቀላቸው ካሣ ተከፍሏቸው እንዲነሱ የተደረጉትንና የድርጅት ቦታ ተሰጥቷቸው ወደ ግንባታ ያልገቡ ግለሰቦች መረጃ አጠናክሮ የመያዝ ችግር መኖሩ፤ በሚሉት በክትትል ኦዲት ወቅት ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድባቸው በተገኙት ግኝቶች ላይ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በመደበኛው የክዋኔ ኦዲት የማሻሻያ አስተያየት መሠረት አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

## 3. የክልሉን አጠቃላይ የግንባታ (ኮንስትራክሽን) አፈጻጸም አስመልክቶ ቀደም ሲል የተሰራውን የክዋኔ ኦዲት እርምጃ አወሳሰድ የተመለከተ የክትትል ኦዲት፤

### 25. በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች፤

**የወልድያ ከተማ ወጣቶች ማዕከል ህንፃ ግንባታ፣**

- የስራ ዝርዝር ሳይዘጋጅና ውል ሳይያዝ የተከናወነውን የተፋሰስና ሌሎችን ጨምሮ በአጠቃላይ መጀመሪያ ከተያዘው ውል በላይ ከ89.4% በብር 934,316.36 በተጨማሪና በአዲስ ውል እንዲጠናቀቅ ሲደረግ ይህን የመፍቀድ ስልጣንና ኃላፊነት የኢ/ከ/ል/ቢሮ ቢሆንም ከስልጣን በላይ በሰሜን ወሎ ዞን ኢ/ከ/ል መምሪያው የተፈቀደ እና ክፍያው የፀደቀ መሆኑ ይህን የፈፀመው ባለሙያ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፤

- ግንባታው በ6 ወራት ለማጠናቀቅ በብር 1,045,089.11 ውል የተያዘ ቢሆንም 516.67 ቀናት በመጨመር በ37 ወራት የተጠናቀቀ ሲሆን ለዘገየባቸው ወራቶች የተፈቀደ ጊዜ ማራዘሚያ የሌለው ሆኖ እያለ ለዘገየባቸው ቀናቶች በየቀኑ ከዉሉ መጠን ላይ ለዘገየበት 1/1000ኛ ብር 1045.09 ለ516.67 ቀናት እየተሰላ ተቋራጩ ተገቢውን ካሳ ለአሰሪ መ/ቤቱ አለመክፈሉ፤

**የነፋስ መውጫ ከተማ አዳራሽ ግንባታ፤**

በኦዲት ወቅት በተደረገ የአካል ምልከታ በተወሰደ መረጃ መሰረት በነፋስ መውጫ ከተማ የተጀመረው የአዳራሽ ግንባታ በአሰሪ መ/ቤቱ፣ በተቆጣጣሪ ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በቂ ትኩረት ባለመስጠቱ የግንባታው መሰረት፣ ግሬድ ቢም፣ ኮለንና ቶፕ ታይ ቢም የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት መጋቢት 30/2004 ዓ.ም ድረስ

ለፀሃይና ለዝናብ ተጋልጦ መገኘቱ ለሚፈለገው አግልግሎት ካለመዋሉም በላይ በህዝብ ሃብት ላይ ብክነት እየተከተለ መሆኑን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

**የምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ጂ+3 የቢሮ ግንባታ፤**

- ለግንባታው ውጫዊ ገጽታ ደህንነትና ውበት ሲባል በኢጣሊያ ሞዛይክ እንዲለጠፍ (Italian mosaic tile) 2000 ካ.ሜ በስራ ዝርዝር ወጥቶ በብር 200.00 ለካ.ሜ ሂሳብ አሸናፊው ተቋራጭ ውል የያዘ ቢሆንም በግንባታው ማጠናቀቂያ ወቅት የኢጣሊያ ሞዛይክ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ከብር 400,000.00 (2000 ካ.ሜx200 ብር) ወደ ብር 1.6 ሚሊዮን ከፍ በማለቱ የኢጣሊያ ሞዛይክ በሐገር ውስጥ የሌለ በመሆኑ፣ ዋጋው በጣም በመጨመሩ ከውጭ ለማስገባት የውጭ የገንዘብ ምንዛሬ ስለሚያስከትልና ግንባታውን በተባለው ጊዜ ማጠናቀቅ ስለማይቻል በሚል ተቋራጩ ባቀረበው ተዓማኒነት የሌለው ማስረጃና ተገቢ ባልሆነ ጥያቄ ምክንያት ጉዳዩን ለክልሉ ኢ/ከ/ል/ቢሮ ቀርቦ እቃው በገበያ ላይ አለመኖሩ ተረጋግጦ በተመሳሳይ የግንባታ እቃ እንዲተካ አስተያየት ቢሰጥም፤

- ተመሳሳይ ሳይሆን ተቀራራቢ ነው በሚል የጥራት ደረጃው ባልተገለጸ ክሊንከር (clinker) በተባለ እቃ የተሰራ ሆኖ ሳለ በክፍያ የምስክር ወረቀት ማረጋገጫ ላይ ግንባታው የተከናወነበት ክሊንከር ሳይሆን ኢጣሊያ ሞዛይክ እንደሆነ ተደርጎ መፈጸሙ ህጋዊነት የጎደለው ከመሆኑም በላይ ለተሰራበት ክሊንከር በ1999 ዓ.ም በጨረታ ወቅት በነበረ ነጠላ ዋጋ መሰረት ሊከፈለው ሲገባ ጨረታ ባሸነፈበት የኢጣሊያ ሞዛይክ ብር 200.00 ለሜ.ካ ሂሳብ ብር 444,000.00 ክፍያ መፈጸሙ፣ አላግባብ ክፍያ እንዲፈፀም ባደረገው ባለሙያ ላይ እረምጃ እንዲወሰድና ገንዘቡም ከስራ ተቋራጩ እንዲተካ አለመደረጉ፣

- የግንባታ ስራዉ ከተያዘለት የማጠናቀቂያ ጊዜ በላይ ለ578 ቀናት የዘገየ ሲሆን ለዘገየበት ቀናት ተቀባይነት ያገኘው የግንባታን መመሪያ ሳይከተል በጊዜአዊ ርክክብ ወቅት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 145 ቀናት ህጋዊ ያልሆነ የዋጋ ንረት መካካሻ ጥያቄ እንዲሁም 90 ቀናት በውል የተያዘውን የኢጣሊያ ሞዛይክ በክሊንከር ለማስቀየር በድምሩ 235 ቀናት በተጨማሪ ግንባታው ከሚጠናቀቅበት ቀን በላይ 92.62% ሲዘገይ የተከናወነው የስራ መጠን 59.31% ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ተቋራጩ የግንባታ እቃ ማቅረብ አለመቻሉ መሆኑ አማካሪው በ01/08/2001 ያቀረበው ወርሃዊ ሪፖርት የሚያመለክት ሆኖ እያለ ምክንያታዊ ያልሆነ የጊዜ ማራዘሚያ በርክክብ ወቅት በአማካሪው ቀርቦ ተቀባይነት በማግኘቱ አላግባብ ለተራዘመበት ጊዜ ተቋራጩና አማካሪው የጋራ ተጠቃሚነት ያላቸው በመሆኑና አሰሪ መ/ቤቱም ጉዳዩን በመቀበሉ የጉዳት ካሳ አለመጠየቁ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ለአማካሪው የተከፈለው የአገልግሎት ክፍያ አግባብ ባለመሆኑ ተመላሽ መደረግ እንደሚገባበት አሳስበናል፡፡

**በደብረ ታቦር ከተማ ህዳር 11 ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ግንባታ፣**

- የቀረበው ዲዛይን፣ የስራ ዝርዝርና የገበያ ዋጋ ባለመከለሱ በሠራተኞች የመጸዳጃ ቤት ግንባታ የ8 ሚ.ሜ እና የ12 ሚ.ሜ ውፍረት ያለው ብረት የሚያስፈልገው መጠን ከ200 ኪ.ግ እና ከ1000 ኪ.ግ በላይ ሆኖ እያለ በስራ ዝርዝሩ እንደቅደም ተከተላቸው 1 ኪ.ግ እና 2 ኪ.ግ ተብሎ በመሞላቱ እጅግ የተጋነነ ነጠላ ዋጋ ተሞልቶ 215.37% እና 541.55% እንደ ቅደም ተከተላቸው የጨመረ ሲሆን የጨመረው የመጠን ለውጥ የደብረ ታቦር ከተማ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ስምምነት ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ስራው በተቋራጩ ፍላጎት ብቻ ከተከናወነ በኋላ በጨረታ ወቅት የአንድ

ኪ.ግ ብረት ዋጋ ብር 19.50 ሆኖ እያለ ብር 700.00 በመሞላቱ ከ125% በላይ ለሚከሰት የስፍር መጠን አዲስ ነጠላ ዋጋ እንደሚተከልለት ስታንዳርድ ኮንድሽን ኦፍ ኮንትራት የሚያዝ ቢሆንም በደ/ጎንደር ዞን ኢ/ከ/ል/መምሪያ በተዘጋጀ የ5ኛ ዙር የክፍያ የምስክር ወረቀት ማረጋገጫ መሠረት ለ1298.50 ኪ.ግ ብረት በብር 700.00 ሂሳብ ብር 908,950.00 በአሰሪ መ/ቤቱ ክፍያ መፈጸሙ አግባብ ባለመሆኑ የክፍያ ምስክር ወረቀቱን ያፀደቀው ባለሙያ ላይ እርምጃ እንዲወሰድበት ሆኖ ገንዘቡ ከተቋራጩ ሊመለስ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

**አዴት ቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋም ህንፃ ግንባታ፣** በኦዲት ወቅት በተደረገበት የአካል ምልከታ በተወሰደ መረጃ መሰረት ለረዥም ጊዜ የተቋረጠው በአዴት ከተማ የሚገኘው የጀኔራል ሜካኒክስና አውቶሞቲቭ ወርክ ሾፖች ግንባታ በተቆጣጣሪ ተቋማት ኢ/ከ/ል/ቢሮ፣ ቴክኒክና ሙያ ቢሮ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ክትትልና ቁጥጥር ማነስ ምክንያት የተቋረጠው ግንባታ ኮለን ወጥቶ ለፀሃይና ለዝናብ ተጋልጦ የተለያየ ዛፍ በቅሎበት ተገኝቷል፡፡

**ፎገራ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የሚያስገነባቸው ጤና አጠበበቅ ጣቢያዎች፣**

በወረዳዉ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እርዳታ የሚገነቡ ግንባታዎች በተያዘዉ የማጠናቀቂያ ጊዜ መጠናቀቅ ባለመቻላቸዉ በጀቱን በወቅቱ ባለመጠቀም ምክንያት የእርዳታ ድጋፍ መቋረጥ ሌላ ተጨማሪ ግንባታዎች እንዳይገነቡ ከማድረጉም በላይ በወረዳዉ የጤና ሽፋን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩን ለጽ/ቤቱ በቀረበው ጥያቄ ምላሽ ላይ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አሁንም በትምህርትና በጤና ጥበቃ መምሪያዎች በተደረገው መጠይቅ ተመሳሳይ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

**የማጠቃለያ አስተያየት፡-**

26. የክዋኔና የክትትል ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች በኦዲቱ የታዩትን ክፍተቶች መነሻ በማድረግና ተገቢ የሆነ አፈፃፀም መርሃ ግብር በማዘጋጀት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰዱ፣ በቀጣይም ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች እንደ መነሻ በመወሰድ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው አሳስበናል፡፡

ስለሆነም በኦዲቱ የተመለከቱትን ግኝቶችና የአሰራር ክፍተቶች በማረም ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ ኦዲቱ እሴት እንዲጨምር በኦዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሚመለከታቸው አካላትና በም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል ክትትል እንዲደረግባቸው እያሳሰብኩ የተከበሩ አፈ-ጉባዔ፤ የም/ቤት አባላት፤የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፤ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በስራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እንዲሁም፤

የመ/ቤታችን የስራ ሃላፊዎች፤ ባለሙያዎችና መላው ሰራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተመላከቱ የስራ ውጤቶች ላደረጋችሁት ጥረት በራሴና በአማራ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ስም ምስጋናየን በማቅረብ ሪፖርቱን በዚህ አጠናቅቃለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

ስመኝ ካሴ እንደሻው (አቶ)

ምክትል ዋና ኦዲተር

**መጋቢት /2009 ዓ.ም**

**ባህር ዳር፣**